ቍጥር 1220

# ሐዋርያው

## ጳውሎስ በግሪክ ሀገር

ተተረጐመ

ከግሪክ ወደ አማርኛ ፤

ከሠርግው ኀብለ ሥላሴ ።

ቆሮንቶስ ግሪክ ።

ታተመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ወ፭ ዓመተ መንግሥቱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ወበዘመነ [illegible] ሢመተ ሊቀ ጵጵስናሁ ለብፁዕ አባ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፲፱ ኛ ዓ፬ ቍ ፫፻፱ መ ፳፻

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D/N Solomon Yoh...
☎ 27 16 09

www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያው

## ጳውሎስ በግሪክ ሀገር

ተተረጐመ
ከግሪክ ወደ አማርኛ፤
ከሥርግው ኃብለ ሥላሴ ።

ቆሮንቶስ ግሪክ ።

ዲያቆን ሰሎሞን
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609

ተነትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ወ፲ ዓመተ መንግሥቱ ለቀዳማዊ
ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ወበክልዕ ዓመተ ሢመተ ሊቀ ጳጳስነሁ ለብፁዕ አባ ባስልዮስ
ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፲፱ ፻ ፵፬ ቀ· ፫፻፱ መ ፳፻

www.ethiopianorthodox.org

ይህች መላውን የሐዋርያው ጳውሎስን ሕይወትና ሥራ አስፍታ የማትገልጽ ትንሽ መጽሐፍ ፤ የ፲፱ኛው ፻ ቅዱስ ጳውሎስ ግሪክን የጐበኘበትና የአቴንን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተበት ክብረ በዓል መነሻ ምክንያት ስለሆነኝ ፤ የግሪክ ሕዝብ በተለየም አቴናውያን የአሕዛብ ሐዋርያ የተባለውን የጳውሎስን ትልቅነት እንዲያጠኑት በማለት ተጻፈች ።

ደራሲው ፤

ደግሞ ለማሳተም የተርጓሚውን ፈቃድ ማግኘት የተገባ ነው ።



ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ።

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ።

የክርስቶስን ወንጌል ለማስፋፋትና በያንዳንዱ ጆሮ ለማድረስ ፤ አንድ ሰው ፈቃድ አግኝቶ በተነሣ ጊዜ ፤ ራሱን ቀድሞ አዘጋጅቶ ለዚህ ሥራ በቂ ሁኖ መገኘት ግዴታው ነው ። ድርጅቱም የወንጌልን ቃል በማጥናትና ሥራውን ከዓለም በመለየት ነው ። ሥራውንም በጀመረ ጊዜ ለሥራው ፊታውራሪ ወይም ግንባር ቀደም ሁኖ ሌሎችን ተከተሉኝ ማለት እንጂ ትእዛዝ ሰጥቶ እርሱ ወደ ኋላ ቢቀር ድካሙ አንዳች ፍሬን የማያሳይ ደረቅ ዕንጨት ሁኖ ይቀራል ።

ምንም እንኳን ዛሬ ይህንን ያህል ቢከፋፈል እንዲህ ተስፋፍቶ የሚታየው የክርስቲያን ሃይማኖት ሲጀመር አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ምን ያህል ደም የፈሰሰለትና የቱንስ ያህል ትግል እንደተደረገለት የሚዘነጋ አይደለም ።

ለመልከም ነገር ሁሉ አጥፊው ብዙ እንደመሆኑ ፤ እንዲሁም በክርስቲያን ሃይማኖት ላይ የተነሡ ጥቂቶች አይደሉም ። ግን እሱም በበኩሉ አልዘነጋም ያንኑ ያህል ጠንካሮች ፤ ጉበዞችና ተከላካዮች በማስገኘት ፤ ለመጣበት አደጋ ሁሉ አቸናፊ እንጂ ተቸናፊ ሁኖ አልተገኘም ።

በመጀመሪያም ከልማደ አሪትና ከአምልኮተ ጣዖት እየተዋጉ ያስለቀቋትን ቦታ ለክርስቲያንነት በማውረስ ታላቅ የማይዘነጋ ውለታ ያለበት አገልግሎት ያቀረቡለት ሐዋርያት ናቸው ። እርሳቸው ም ስለሃይማኖት የነበራቸው ፍቅር ፤ ግምት የማይሰጠው እጅግ ስለነበረ ፤ በሞታቸው እንኳን ሳይቀር ፤ አገልግሎታቸውን ገልጠዋል ። የእውነተኛ ፍቅር መደምደሚያው ለወዳጅ ተላ

www.ethiopianorthodox.org

ልዩ መሞት ነው ። ስለ ሃይማኖት የተቀበሉት መከራና አሟሟት ልዩ ልዩ ነው ። «የገረፍዋቸው ፤ የዘበቱባቸው ፤ አሥረው የያዝዋቸውም አሉ ። በመጋዝ የሰነጠቋቸው ፤ በድንጊያ የወገሩዋቸው ፤ በሰይፍ መትተው የገደሏቸው ፤ ማቅና ፀጕር የፍየልም ሌጦ ለብሰው የዞሩ አሉ ፤ ተቸገሩ ተጨነቁ ይህ ዓለም የማይገባቸው እሊህ መከራን ተቀበሉ ። ዱር ለዱር ፤ ተራራ ለተራራ ፤ ዋሻ ለዋሻ ፤ ፈረፈር ለፈረፈር ዞሩ ። እሊህ ሁሉ በሃይማኖት ሰማዕት ሆኑ እያለ ቅዱስ ጳውሎስ ይተነትናል ። (ዕብ ፲፩ ፴፯ ። ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ስለ ሃይማኖት ብለው የተቀበሉት እንዲህ ያለውን መከራ ነው ። ከእነሱም አንዱ ሐዋርያው ጳውሎስ በተለየ በአምላክ ፈቃድ ከሕገ ኦሪት ቀናተኛነት ተጠርቶ ፤ የተቀደሰ ዕቃ ሁኖ በአሕዛብ መካከል ስሙን የመሸከም ሀብት የተሰጠው ነው ። እርሱም በመንፈስ ከአገኘው ሌላ በተፈጥሮው ብልህ ዘዴ ዐዋቂ ፤ ለመከራ እሺ በጂ የማይል ጉብዝና ቈራጥ ነበር ። ለዚህ ታላቅ ክብር ከመጀ ጀምሮ እንዲተገበ ለማመልከት «ከእናቱ ማኅፀን ብሎ» እራሱ ያስረዳናል ። (፩)

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሥራው እሱው በመልእክቶቹ ስለ ሚተርክ እርግጠኛ አሳብ ይሰጠናል ። (ለምሳሌ ፤ ሐዋርያነቱ ለማን እንደሆነ እንዲህ ሲል ወደ ኤፌሶን በጻፈው መልእክቱ ሙሉ አሳብ ይሰጠናል ። «ለአሕዛብ አስተምራቸው ዘንድ ብሎ» (፪)

ይህች መልእክት የበርናባስ ናት እንጂ የጳውሎስ አይደለችም በማለት ብዙ መጠራጠር በሊቃውንት ዘንድ አለ ። ቢሆንም ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ለጳውሎስ በመስጠት አሳቡዋን ታጸናለች ።

፩ ገላ ፩ ፲፭
፪ ፫ ፰



በዚህ መሠረት የሐዋርያ ጒዞውን ወደ ኤውሮፓ ቀጥሎ ፤ መጀመሪያ የወንጌልን ፋና በግሪክ ላይ አበራ ። ግሪክም ይህ ትልቅ ውለታ እንደሆነ በመገንዘብ ለወሮታው መታሰቢያ በዚህ ዓመት ምሕረት (፲፱፻፵፫) መጨረሻ በሰኔ ወር የ፲፱ኛውን መቶ ፤ ወዲህ የመጣበትን ክብረ በዓል የዓለም ቤተ ክርስቲያናት አባሎች በአሉበት በሚገባ አከበረች ። በዚሁ ጊዜ ይህች መጽሐፍ ከዚህ ቀደም ብሎ እንደ ተነገረው አንድ መምህር ፤ የግሪክ ሕዝበ ክርስቲያን እንዲያጠናት በማለት ጻፋዋት ። እኔም ለማንበብ ገዝቻት ሳለ ከተመለከትኋት በኋላ ወደ አማርኛ ብትመለስ ጠቃሚ አድርጌ ስለቆጠርኋት ወደ አማርኛ እንድትተረጐም አደረግሁ ። ሕዝበ ክርስቲያናት በማንበብ ይጠቀሙባት ዘንድ ምኞቴ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ማ ስ ታ ወ ሻ ።

ደራሲው ከመጻሕፍት የሚጠቅሳቸውን ቃላት የሚገኙበትን ምእራፋትና አኀዞች ለማመልከት ሲፈለግ ፤ በቅንፍ በቍጥር ከአመለከተ በኋላ ከግርጌ ይጽፋል ። በዚሁም ላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንግዳ የሆኑ ነገሮች አልፎ አልፎ በመገኘታቸው ፤ አንባቢን አለመረዳት እንዳያነቅፈው በማለት ፤ እኔም አስፈላጊዎቹን እንዲሁ ስለአመለከትሁ በቅንፍ ቍጥር (፩) በሚያይበት መሥመር ያኔውኑ አዘቅዝቆ ከታች እንዲመለከት ለአንባቢ ይታወሰው ።



## ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የግሪኮች በነበረችው የቂልቅያ ዋና ከተማ የዕውቀት ፤ የጥበብና የንግድ መደብር በነበረችቱ በጠርሴስ ተወለደ ። ይህች ከተማ በመጀመሪያ በጥበብና በዕውቀት ከእስክንድርያና ከአቴን ጋር ተወዳዳሪ ሁና ነበር ። ስለዚህ ትዕቢት ባልተፋ ላቀለበት ኵራት እራሱጳው ሎስ እንዲህ ይላል "እኔስ አይሁዳዊ ነኝ ። የተወለድኩበትም ሀገር ጠርሴስ የታወቀች የቂልቅያ ከተማ ናት „ (፩) ።

ከመመለሱ ብዙ ዓመታት ቀደም ብሎ ጳውሎስ በጠርሴስ ስለኖረ ፤ የከተማይቱ የግሪክ ስሜት በኅሊናው ተቀርጾበት እንደ ነበር አያጠራጥርም ። በያለበት በተበተኑ ዕብራውያን እንደሆነ ፤ እንዲሁም ጳውሎስ የጻፋቸውን መልእክቶች ከማጥናት የተነሣ ፤ በጠቅላላው ዛሬ እርሱ የግሪክን ቋንቋና የኑሮአቸውን ልማድ አጥንቶላቸው እንደ ነበር ታወቀ ። የልዕልናው ፈቃድ ትልቅ አእምሮ ያለው አድርጎ የወንጌልን ትምህርት እንዲሰብክና ክርስቲያንነትን እንዲያስፋፋ ለይቶት ስለነበር ፤ በግሪክ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆን ተገባው ። ስለምን ? ሥሥሬጐሪዮስ የሚባለው ታሪክ ጸሐፊ እንደሚለው « መንፈስ ቅዱስ በግሪክ ቋንቋ እንዲናገር ስለረዳው በማናቸውም ተዘጋጀ። ስለዚህ ቅዱስ ዓላማ በምሥራቅ በበዛው ቦታ የግሪክ ቋንቋ ይነገር ስለነበር ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ተገኘ ።

በሮምና በዕብራውያን መካከል በዚያን ዘመን በሚደረገው ንግድ ፤ ጥቅም ያደርጉት የነበር ቋንቋ የግሪክ ነው ። በበዛውም ቦታ በጳለስቲን ይህ ቋንቋ ይነገር ነበርና ስለዚህ ቅዱስ

---

፩ የሐዋርያት ሥራ ፳፩ ፴፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስ (የግሪክ ስሜት ያለው ዕብራዊ) ይህን ቋንቋ ዐውቆ ለመስበኪያና መልእክቶችን ከአለፉት ነገር ዐዋቂዎች ንግግር እየጨመረ ለመጻፊያ ጥቅም ያደረገው የግሪክ መንፈስ እንዳለው ምስክር ይሆናል ። (፩)

የተወለደበት ዘመን በ፶፰ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ወደ ፊልሞና በጻፈው መልእክት እንደምንረዳው እራሱን ‹ ትልቅ» (የመጀመሪያ) ብሎ የሚጠራውን ተከትለን ምናልባት ከክርስቶስ በኋላ በ፬ ዓመት ሳይሆን አይቀርም ። ከዕብራዊ ቤተ ሰብ ከብንያም ነገድ ነበር ። ቆይቶ ግን የሮማውያን ዜጋ (ሮማዊ) ለመሆን ችሏል ። (፪

አንድ ሰው ሮማዊ ለመሆን በመግዛ ወይም ሮማውያንን በማገልገል ፡ አለዚያም ሮማውያን እንደቸርነት እንዲሁ ይሰጡ ነበር ። ግን ከዝቅተኛ ደረጃ (ከደኻ ቤተ ሰብ የሆኑ) ለማግኘት አይችሉም። ይህ የጳውሎስ ሮማዊ መሆን የተለየ ትልቅ ጥቅም ያለው ሙሉ ስሜት ነበር ። የወንጌልን ቃል በሚዘሩበት ጊዜ ከደረሰበት ፈተና ብዙ ጊዜ አዳነው ። በደረሰበትም መከራ ትልቁ የሐዋርያነቱ ሥራ ተቋርጦ ቢሆን ሊታረም የማይቻል ጉዳት በቤተ ክርስቲያን ወደቀበት ማለት ነበር ።

የመጀመሪያ ስሙ ሳውል ወይም እንደ ግሪኮች አጠራር ሳብሎስ ነበር ። በኋላ ግን የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ ጉዞ ከደረገበት አንሥቶ በሚከተለው እንደምናየው በሮማዊ ስሙ ጳውሎስ እየተባለ ይጠራ ጀመር ። (፫) ከዕብራዊ ወገን የአይ

፩ የሐዋ ሥራ ፲፯ ፳፰ ።

፪ የሐ ዋ ሥራ ፳፪ ፳፱ ።

፫ የሐ ፲፫ ፱ ።



ሁድ ነገድ እንደመሆኑ ፤ የዕብራውያንን ትምህርት ማወቅና በረቢናውያን ቋንቋ ሕገ ኦሪትን ማጥናት ተገባው ።

በዚህ ምክንያት በጠርሴስ የመጀመሪያውን ደረጃ ትምህርትና ሕገ ኦሪት የተጻፈበትን ዕብራይስጥን ከጠንቃቃ ፈሪሳዊ (፩) አባቱ ከተማረ በኋላ ገና ወጣት ሳለ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ አንድ ትልቅ የሕግ መምህር ስሙንም ገማልያል ወደ ሚሉት ተላከ ። ይበልጥ የጥበብ ችሎታ ያለው ፤ አእምሮው ትልቅ ፤ ልበ ሰፊ ፤ ምኞቱ መልካም መሆኑን በዚሁ ጊዜ አሳይቷል ።

ገማልያል የግሪክን ትምህርት ዐዋቂ በመሆኑ ተማሪዎቹ ግሪክ ይማሩ ዘንድ ከማበረታታት ዝም አይልም ነበር ። በዚህም ጊዜ ጳውሎስ ከግሪክ ሕግ ዐዋቂ መምህሩ ሊጠቀም ነው።

የግሪክን የፊሎሶፊ ትምህርት አጠና ማለት ነው ። የዕብራውያን ሲያያዝ የመጣው አፈ ታሪክ እንደሚያረጋግጥልን በረበናውያን ትምህርት ቤት የግሪክ ዕውቀት ተስፋፍቶ ነበር ። ጳውሎስ ረበናዊ ከሆነ በኋላ ለዕለት እንጀራ ማግኛ በዚያን ጊዜ የነበሩ ዕብራውያን አንድ ጥበብ ለልጆቻቸው ማስተማር ልማድ ስለነበራቸው እሱም እጁን ድንኳን በመስፋት ጥበብ አፍታታው ።

፪ ፈሪሳውያን ቀናተኞች ፤ ዕብራውያን ልማዳቸውንና የውጭ አምልኮታቸውን ደግሞም የሙሴ ሕግ የተጻፈበትን የሞተ ቋንቋቸውን እጅግ የሚወዱ ፤ ከሌሎች የተለዩ ክፍል ናቸው ። እነሱ የሚበልጡት ባለጸጎች በመሆናቸው በሕዝቡ ላይ ሥልጣን ነበራቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ የድንኳን ስፌት ጥበብ እንደ ጣሪያ ያለውን ሽፋን ከጠጕር ጨርቅ ወይም ከቆዳ አጋጥሞ መስፋት ነበር ። ድንኳኖቹንም ከአንድ ቦታ ወደሌላ ለማዛወር የማያደክም ለዘላኖችና ለወታደሮች ወይም ለመንገደኞች ጠቃሚ ነበር ።

በዚያን ዘመን ጠርሴስ በድንኳን ስፌት ዝነኛነቷን አሌ የሚል የለም ። ስለዚህ ሳይሆን አይቀርም ጳውሎስ ሌላ በመምረጥ ፈንታ ይህን የመረጠው ። (፩)

የክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነ በኋላ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው በሁለተኛው መልእክት ሲጽፍላቸው እንዲከተሉት አርአያ ለመሆን ከእጁ ሥራ ባገኘው ራሱን መደገፉን ይገልጽላቸዋል ። "ሥራ ሳንሠራ የሌላውን እህል አልበላንምና እናንተን እንዳናስቸግር ሌትና ቀን ሥራ እየሠራን እንደክማለን እንጂ ፤ ለእኛ የማይገባን ሁኖ አይደለም ትመስሉን ዘንድ ምሳሌ እንድንሆናችሁ ነው እንጂ» (ተሰ ፫ ቀ ፱) ።

ገማልያል ስለብልህነቱ አዲስ ነገር ወዳጅ እንደመሆኑ የክርስቶስ የሥውር ተማሪ ነበር ተብሎ እስከ ታመን ድረስ የሚደነቀው ፤ የተማሪውን (የጳውሎስን) ቅናትና ሌሎችን ለማገንቀፍ በሕሊናው የተጻፈውን አሳብ ለማጥፋት ሳይሆንለት ቀርቷል ።

(፩) የረበናውያን ክፍል የታየው የሰሎሞን ቤተ መቅደስና የክህነታቸው ሥልጣን ከጠፋ በኋላ ነው ። እሊሁም ከሕዝቡ መካከል ችሎታ ያላቸው የሙሴን ሕግ እየተረጐሙ ለሕዝቡ እንዲያስተምሩና የሃይማኖት መሪ ሁነው ሕዝቡን እንዲጠብቁ ይጠሩሉ ። ለእነሱም የዕለት እንጀራቸውን ማግኛ የሚሆን አንድ ጥበብ ለምዕራባት ሸክም እንዳይሆኑ በማለት ያውቁ ዘንድ ይፈቅዳል ።



## የጳውሎስ ኑሮ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ።

በትክክል አሪትንና ጽሑፋዋን ለመጠበቅ በሙሉ አቅሙ ይደክም ነበር በዚሁም እንዴት ደስ ይለው እንደነበር እሱው ራሱ በኋላ ወደ ሮሜ በላከት መልእክቱ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ነው ሲል ይገልጻል ። በዚህ ምክንያት የክርስቶስ ትምህርትና የክርስቲያኖች ጸር ነበር ። የታሠረ ስሜቱ ይህ አዲስ ሃይማኖት ቈይቶ የይሁዳን ሃይማኖት የሚያጠፋ መሆኑን ስለተረዳ እንዲቃወም በል በል ይለው ነበር ። ስለዚህ በመላ ኃይሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት መነሣቱን እሱው እራሱ ወደ ገላትያ በጻፋት መልእክቱ ይገልጻል ። ገላ ፩ ፲፫ ።

በዚህም ምክንያት ቀዳሚ ሰማዕት እስጢፋኖስ በድንጋይ ሲደበደብ ተመልካች ብቻ አልሆንም ። በነገሩ ኀብቶበት የደብዳቢዎቹ ልብስ ተሸካሚ ሆነ ። ቅዱስ ሉቃስ የእስጢፋኖስን (፩ አሳብ) ቈይቶ በአይሁድ እጅ በድንጋይ መደብደብን ያስከተለውንና የክርስቲያኖችን መበተን) ፤ እንደሚገባ አድርጎ ይተርካል ። ቈይቶም እየበዛ እንደሔደና ምን ፍጻሜ እንደሆነ በሐዋርያት ሥራ ይጽፋል ። ቅዱስ ጳውሎስም ሥራውን በዚያች በድንቂቱ ወደ ጌታ በተመለሰበት ቀን እንዲህ ሲል አምኑዋል ። የሰማዕትህንም የእስጢፋኖስን ደም በፈሰሱ ጊዜ ከርሳቸው አንዱ ሁኜ ከዚያ ቁሜ የገዳዮቹን ልብስ እጠብቅ ነበር (የሐ ሥራ ፳፪ ፳) በመልእክቶቹም ደግሞ ለምሳሌ ፤ ወደ ገላትያ በላከት ብአይሁዳዊነት ሳለሁ የነበርሁበትን የቀድሞ ግብሬን ሰምታችኋል ። ቤተ ክርስቲያንን ሳሳድድና እርሷንም ሳፈርስ

(፩) እስጢፋኖስ ፤ ከሰባቱ ዲያቆናት የመጀመሪያዩቱ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መርጠ ሐዋርያት ከሾሟቸው አንዱ ነው ። በአይሁድ በድንጋይ ተደብድቦ የሰማዕትነትን ሞት በ፴፫ ከክርስቶስ በኋላ ተቀበለ ።

www.ethiopianorthodox.org

እንደነበርሁ ። በወገኖቼም ከባልንጀሮቼ ይልቅ በአይሁድ ዘንድ ከብሬ እንደነበር ለአባቶች ሕግ እጅግ ቀናተኛ ነበርሁ» ቀዳ ቆሮ ፲፭ ፱ ።

አንበሳ ወይም ተኩላ የበግ መንጋን እንዲያድን እንዲሁም እሱ ክርስቲያኖችን ማንንም ሳይመርጥ ሴትም ብትሆን ቀሉ ያድናቸው ነበር ።

የማይታሰብ የማይለወጥ ጨካኝ አሳዳጅ መንፈሱ አሁን ወደሌላ ሊመራው ነው ። በኢየሩሳሌም የሠራው ክፋት ለጨካኝ ሕሊናው አጥጋቢ መስሎ ስላልታየው ከኢየሩሳሌሙ ሊቀ ካህናት የፈቃድ ደብዳቤ ጠይቆ አገኘ ።

በደማስቆ በክርስቶስ ያመኑትን ያገኘውን ያህል አሥሮ ያመጣቸው ዘንድ ። ግን መሲሕ ተሰቀለ ተብሎ የሚነገረው ትምህርት ለአይሁድ ሃይማኖት ዕንቅፋት መስሎ የታየው ይህ ለአባቶች ሕግ ቀናተኛ አንዳች ጉዳት ለመፍጠር ችሎታ ሳያገኝ ቤተ ክርስቲያንን ያፈርስ ዘንድ ጉዞውን ወደ ደማስቆ ቀጠለ። ከዚህ ቀደም ብሎ የኢየሩሳሌምን እንዳፈረሰ በታላቅ ደስታ ሔዶ ማሳደዱን ሊያስፋፉ ። ደግሞ ሌላ አገልግሎት ለአባቶች አምላክ ያቀረበ መስሎት ነው ።

## የደማስቆ ራዕይ ።

በከተማይቱ ደጃፍ ሲደርስ በሚያስደንቅ ራዕይ ጌታ ተገለጸለት። ቀጥለንም እንደምናየው የጳውሎስ ልብ የተለወጠ ይሆናል። እነሆ ወንጌላዊው ሉቃስ እንዴት እንደሚጽፍ ፤ ሲሔድም ወደ



ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ላይ ከሰማይ የብርሃን ፀዳል አንጸባረቀና በምድር ላይ ወደቀ ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ የሚል ድምፅም ሰማ ።

«አንተ ማነህ ጌታዬ» ሲል ጳውሎስ ጠየቀ

«አንተ የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ አለው» ጳውሎስም ከማድነቅ ጋር ፍርሃት ተመልቶበት እንዲህ አለ ።

«አቤቱ ጌታዬ ምን አደርግ ዘንድ ትሻለህ» ጌታም «ተነሥተህ ወደከተማ ሒድ ታደርገው ዘንድ የሚገባህን ከዚያ ይነግሩሃል» አለው ። (፩)

ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ሊታሰብ የተገባው ለውጥ ከዚህ ቀጥሎ ላለው ኑሮ የሚሆን በልቡ አደረ ።

አብረውት ይሔዱ የነበሩት ማንንም ሳያዩ ድምፅ ብቻ ይኸውም ምን እንደሚል ሳይረዱት ስለሰሙ ታላቅ ፍርሃት ወደቀባቸው ። ቄይቶም ጳውሎስን አነሡት ዓይኖቹም ምንም የተከፈቱ ቢሆኑ አያዩም ነበር ። አንሥተውም ወደ አንድ ክርስቲያን ቤት አገቡት ። በዚያም ፫ ቀን ዕውር ሆኖ ሳይበላም ሳይጠጣም ተቀመጠ ። ሐናንያ የሚባል ክርስቲያን በዚያ ሳለ በአምላክ ትእዛዝ በገቦኘው ጊዜ "ወንድሜ ሳውል ሆይ ስትመጣበመንገድ የታየህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይመላብህ ዘንድ ላከኝ,, አለው (፪) ከዚህ ንግግር በኋላ ጳውሎስ ተጠመቀና እህል ቀመሰ ።

፩) የሐዋ ሥራ ፱ ፫-፯

፪) የሐዋ ሥራ ፱ ፲፯-፲፱ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ የደማስቆ ራዕይ የፌተኛውን ጠባይ በኑሮው ያደርገው የነበረውን ለወጠና ወደ ፍጹም ጠቃሚ ሕይወት መራው ። ያ ቀናተኛው ፈሪሳዊ ወደ ክርስቲያን ሃይማኖት ተለወጠ ። ከአሁን ጀምሮ ትልቁን መልእክቱንና የታቀደውንም ከፍ ያለ ፕላን ፤ በአምላክ ፈቃድ ተረዳ ።

ይህ ግሩም ብርሃን (በራዕይ ያየው) ከኃጢአት ዐመፃ አነጻ ውና ያንን ጨካኝ አሳዳጅ ፤ የክርስቶስ ትልቅ ሐዋርያ እንዲሆን ለወጠው ።

## ጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያ ።

ጌታ አናንያስን እጁን በጳውሎስ ላይ ጭኖ ዓይኑን እንዲከፍትለት በአዘዘው ጊዜ እንዲህ አለው « ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነውና ሒድ » (፩) በእርግጥም ከተፈወሰና ከተጠመቀ በኋላ በሚያስገርም ቈራጥነት በሚከተለው እንደምናየው ጳውሎስ በደማስቆ በሚገኙት ምኵራባት የክርስቶስን ስም ይሰብክ ጀመር ። አሁን ጳውሎስ የክርስቶስን ስም ሲጠራ ደስታ ይሰማዋል ። ከዚህ ቀደም የእርሱ ተወዳጅ የሆኑትን ያሳደደው ያልተፈቀደ ሥራና ትልቅ ጥፋት እንደሆነ ተረዳው ።

እራሱ ወደ ቆሮንቶስ በላከት በመጀመሪያይቱ ጠማር እንደሚገልጸው "ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ የተለየ ይሁን (፪)"

ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ጥቂት ቀኖች ብቻ እየሰበከ በደማስቆ ቈየ ። የቀድሞ ጠባዩን (ቀናተኛ ፈሪሳዊ የነበረውን) ማረምና ለአዲሲቱም ሕይወት ለክርስቶስ ቀናተኛ በመሆን ተስማሚ ይሆን ዘንድ ወደ ዐረብ (ጸጥታና አእምሮው ወደ ሚሰበሰብበት ቦታ) መጣ ።

(፩) (የሐዋ ሥራ ፱ ፲፭)
(፪) ቆሮ ፲፮ ፳፪ ።



፫ ዓመታት ያህል በዚህ ከቈየ በኋላ ፤ ወደ ደማስቆ ተመልሶ በድንብ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚያነጥረውን እውነተኛ ትምህርት ጀመረ ።

ነፍሱም ፍቅረ ክርስቶስን ስለተመላች በቈራጥነት የክርስቶስ ስም እንዲታወቅ ውድድሩን ጀመረና አንዳች ፍርሃት ሳይሰማው በወገኖቹ ፊት በደማስቆ ምኵራባት ይሰብክ ጀመር ።

ይህንን ትምህርቱን አይሁድ በሰሙ ጊዜ ልክ እንደ ነፍሰ ገዳይ ያህል በመጥላት እንዲህ አሉ ። "ይህ በኢየሩሳሌም ይህንን ስም የሚጠሩትን ሁሉ ያጠፋ የነበር አይደለምን" ? ስለዚህስ እያሠረ ወደ ካህናት አለቆች ይወስዳቸው ዘንድ ወደ ዚህ መጥቶ አልነበረምን ? (፩) ,, ጳውሎስም ምንም ይህን ያህል ቢጠሉት ጥቂትም ሳይፈራ ያ እነሱ የሰቀሉት እሱ ክርስቶስ መሆኑን አስረዳቸው ፤ ከዚህም ምክንያት ጠላቶቹ ሊገሉት ቈረጡ ። በዚያ የነበሩ ክርስቲያኖችም ረዱትና ከሞት አድነው ወደሌላ ላኩት ።

ከዚህም አደጋ ከዳነ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም የሕገ አሪት መዲና ወደሆነበት በበኩሉም ክርስቲያንነት በ፴፫ ከክርስቶስ በኋላ የተመሠረተችው የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሥር ሰዳ ነበር ።

ጳውሎስ ያ የቀድሞው የማይፈራ ጨካኙ አሳዳጅ አይደለም ፤ በመላው አቅሙ ለአዲሲቱ ሃይማኖት ተከላካይ ጠባቂ ሁኖ እንድትታወቅ የሚጥር ነው እንጂ ።

እዚያም በደረሰ ጊዜ ነፍሱ መራራ ስሜትን ከመቅመስ ተግ አላለችም ። እሱም የነበረበት ፤ እስጢፋኖስ የተወገረበት ድንጋይ ተቈልሎ አየ ። ደግሞም ፈሪሳውያንና በግሪክ የሚኖሩ ዕብራውያን የአባቶችን ሃይማኖት አሳልፎ ሰጠ በማለት

(፩) የሐዋ ሥ ፱ ፳፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

የቱን ያህል እንደሚጠሉት ታሰበው ። ከሐዋርያት ጋር መተዋወቅ፡ ከእነሱ ጋርም ሠራተኛ ሁኖ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወንጌልን በዓለም ለመዘርጋት የሚቻል በመሆኑ ፤ ወዲህም በእርግጥ መመለሱን ሀውቀውለት በፍቅር መተሣሠር የተገባ ሁኖ ታየው ። ፊት እንደዚያ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረ አሥጊ አሳዳጅ መመለሱን ሐዋርያት ስላላመኑለት ለመጀመሪያ ሊገናኙት አል ፈቀዱም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያናቸውን ከሚመጣበት ጥፋት ለመጠበቅ ሲሉ ነው ። ግን ለሐዋርያት ፣ ስለ ብዙ ፍቅሩ ፣ ለኢየሩ ሳሌም ቤተ ክርስቲያን በጣም የታወቀና የታመነ ሰው (፩) ለጳው ሎስም ወዳጅ የነበረው የመመለሱን ነገር እንዴት እንደሆነ ከሥር እስከ ጫፍ ስለ ተረከላቸው የታመነ እርግጠኛ ወሬ ስለ ጳውሎስ መመለስ እንዳገኙ ስለተገነዘቡና በእግዚአብሔር ጥሪ እንደ ተመለሰ ስለተረዱት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ተቀበሉት ።

በዚህ ጊዜ ጳውሎስ የጌታ ሐዋርያ በመሆኑና ለመመለ ሱም የማያጠራጥር እርግጠኛነቱን ለማስረዳት ስለ ጌታ ትንሣኤ ከአይሁድ ጋር ተከራከረ ።

ያለፍርሃት የሚያስተምረው ትምህርት ፤ እንደምንም ብለው እንዲያጠፉት በአይሁድ ላይ አሳብ እንዲቀሰቀስ ምክንያት ሆነ ። ይህም አደጋ ከመድረጉ በፊት ሐዋርያትና በኢየሩሳሌም ይገኙ የነበሩ ክርስቲያኖች በቶሎ በጳለስቲን ወደ ምትገኘው ቂሳርያ ላኩት ። ከዚያም ወደ ሀገሩ ወደ ጠርሴስ መጣ ።

(፩) ይህምሰው ከጳውሎስ ጋር የሐዋርያነትን ሥራ ያከናውን የነበር የቆጵሮሱ በር ናባስ ነው ። በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞ በቆጵሮስና በታናሽ እስያ ጳውሎስን ተከትሎ ስለ ክርስቲያንነት ሃይማኖት ትልቅ አገልግሎት አቅርቧል ። ቈይቶ ግን ሰብቻው ከማርቆስ ጋር ሐዋርያዊ ጉዞ አደረገና በቆጵሮስ የሰማዕትነት ሞት ተቀበለ።



በዚሁም ላይ ከኢየሩሳሌም እንዲወጣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር ።

ስለምን ? በቤተ መቅደስ ሲጸልይ በራዕይ ጌታ ተገልጾ እን ዲህ አለው «ስለኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህምና ከኢየ ሩሳሌም ፈጥነህ ውጣ» (፩) ትልቁን የሐዋርያነቱን ሥራ ጌታ ሲናገር ይህ ፪ኛ ጊዜ ነው ። እንዲህ ሲል ። «በሩቅ ሀገር ወደ አሉት አሕዛብ እኔ እልክሃለሁና»

ጳውሎስ ከሐዋርያት እንደ አንዱ ከተቈጠረበትና ለወንጌል መልእክተኛ እንዲሆን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ እንደሚከተለው በንግግርና በመልእክት «የአሪትን የብረት አጥር ሰበረውና በውስጡ የሕይወት ዛፍን ተከለ ። አዲሱ ሐዋ ርያ በመላው ዓለም ለሚኖሩት ፤ የአሕዛብ መምህር ተብሎ የተሰየመው በሚገባው ነው» (፪)

በጠርሴስ ብዙ ቀኖች ተቀምጦ በርናባስን ካገኘ በኋላ ወደ አንጾኪያ መጥቶ ፣ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያውን የክርስቲያኖች ማኅበር መሠረተ ።

እሊህ ሁለቱ ሐዋርያት በሚገባ እየሠሩ አንድ ዓመት ሙሉ ስለኖሩ ፤ የግሪክ ከተማ የነበረችውን አንጾኪያን ትልቅ የክርስቲያን መደብር አደረጓት ። እዚህ ነው በመጀመሪያ የክርስ

፩ የሐዋርያት ሥራ ፳፪ ፲፰ ።

፪ የፓፓሪጎፑሎስ ታሪክ በ፪ተኛው መጽሐፉ ገጽ ፹፰ ተመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org

ቶስ ተከታዮች ክርስቲያን ተብለው የተሰየሙት ፡ ጳውሎስም ዋናውን የክርስቲያን ትምህርት በክርስቶስ ሬት አረማዊ አይሁዳዊ በመባል አንዳች መ ለዩ ፡ እንደሌለ አስረዳቸው ።

« በዚህም አይሁዳዊ ከአረማዊ ፤ ቤተ ሰብእ ከጌታ ፡ ጌታ ከቤተ ሰብ ወንድ ከሴት ፤ ሴት ከወንድ መለየት የለም በኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችሁም አንድ ናችሁ እንጂ »

ይህችም የክርስቲያንነት መዲና ከሆነችው ከአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያነቱን ሥራ ያን ጊዜ የሮማ ግዛት በነበሩት ሀገሮች ላይ ለማስፋፋት መነሻው ሆናለች ።

## የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ ።

## ሥራ ጠቅላላ አስተያየት ።

ወደ ሮሜ በላከት መልእክቱ ቅዱስ ጳውሎስ በጐበኛቸው ሀገሮች የሰበከው የወንጌል ቃል በከንቱ እንዳልቀረ ለማመልከት በአጭሩ እንዲህ ሲል ያነሣቸዋል ። «ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ ኢልያሪከአውራጃ የክርስቶስን ትምርት ፈጸምኹ (፩) ።

በመጀመሪያው ምዕራፍ በዚሁ መልእክት ሐዋርያው የሔደባቸውን የአሕዛብ አገሮች የሃይማኖትና የልማድ

፬) ኢልያሪኮ ከኢየሩሳሌም ደቡባዊ ምሥራቅ የምትገኘው የጥንት ጠንካራ ከተማ ናት ። ግን ጳውሎስ ያስተማረው የአሕዛብ መምህር እንደተባለው በትንሽ እስያና በኤውሮፕ በመሆኑ ፤ ኢልያሪኮ በማለት ፈንታ ኢሊሪኮ ብሎ ማንበብ ነው ። ይኸውም ከሮማውያን ፬ቱ ያአውራጃ ግዛት አንዱ ነው ። በአድሪያ ባሕር አካባቢ ያሉትን ሀገሮች ይይዛል ። በላቲን ኢሊሪኩም የእንግሊዙም ሐዲስኪዳን ይህንኑ ተከትሎ II lyr -i- cnm ይለዋል ። በግሪግ ኢሊሪያ ።



ስሜታቸውን ከተመለከተ በኋላ በትንሽ መሥመሮች እንዲህ ሲል ይገሥጻቸዋል ። «ጽድቅን ዐውቀው በኀጢአት በሚለውጡ በደለኞችና በኀጢአተኞች ሰዎች ሁሉ ላይ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መቅሠፍት ከሰማይ ይመጣል ። እግዚአብሔርን ማወቅ በእነሱ ዘንድ የተገለጸ ሊሆን እግዚአብሔር ዕውቀትን ገልጾላቸዋልና ዓለም ሳይፈጠር የማይታወቅ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይታወቃል ። በማሰብና በመመርመር ዐላውቅም ብለው ምክንያት እንዳያገኙ ኃይሉና የዘለዓለም ጌትነቱ እንዲህ ይታወቃል ። . . . «(፩)

በዚህ ንግግር የያንጊዜውን የአሕዛብን ሃይማኖትና ጠባይ ፈጽሞ የከፋ እንደሆነ ይገልጻል ። ይህንኑ ቅዱስ ጳውሎስ ከረዳቶቹ ጋር ማሻሻል ጀመረና ከእስራኤል ስም ሁሉ እጅግ ይጠሉት የነበረውን የክርስቶስን ስም እንዲቀበሉትና እንዲያምኑበት አደረገ ።

እርግጠኛ አሳብ ነው ። ጳውሎስ ከመመለሱ በፊት ወንጌል ለአሕዛብ መሰበክ ተጀምሮ እንደነበረ ፡ የሚያስረዳ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ቀደም ብለን እንዳየነው በርናባስ አሕዛብን ይመልስ (ያሳምን) ዘንድ ወደ ሶርያ ዋና ከተማ ወደ አንፆኪያ ልከው ነበር ። ግን ጳውሎስ ጥበብ በተመላ ፈሊጥ የአሕዛብን ሀገር ለመዞር ቈረጠና እስከ ዕለተ ሞቱ ፬ ሐዋርያዊ ጉዞ አደረገ ።

(፩) ሮሜ ፲፰—፲፱ ፬ ም ፩ ፲፰

www.ethiopianorthodox.org

ይህንንም እንዲህ ያለ ትልቅ ሙያ በዓለም ታሪክ የተቈጠረ ውን ተግባር ፡ ከግቡ ለማድረስ ብዙ ዕንቅፋት አግኝቶት ነበር። ግን በመጀመሪያ በብልህነቱ በአገኘው ዘዴ ዕንቅፋቱን ስለሚያ ጠፋው አሰናክሎ ሊያስቀረው አልቻለም ።

የሐዋርያዊ ጉዞው ፲፬ ዓመታት የፈጀ ሲሆን የቱን ያህል ወንጌል በዓለም ላይ እንደተሰበከችና የቱንስ ያህል አብያተ ክር ስቲያናት እንደተመሠረቱ አብዝቶ ለመገመት ይቻላል ።

ሁልጊዜ መልክም አሳቡን የሚቀንስበትን መከራውን ፡ ሥራ ወዳድ፣ ፈጣን መሆኑንና በጉዞውም ያደረጋቸውን ፣ ጠል ያለበ ቸው ስብከቶቹን ስንመለከት ፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «የማያ ርፍ የቤተ ክርስቲያን የመስቀል ያፍ ያለው ይታሰበናል ። (፩)

ስለምን? ለያንጊዜ በጣዖት አምልኮት ክረምት ውስጥ ይሠቀይ ለነበረው ዓለም መጺው የሆነችቱን አዲሲቱን ሃይማኖት አምጥ ቷልና ። ትልቁ ባስልዮስም እንዲህ ሲል ይጠራዋል። «መንገደኛ» ሃይማኖትን የተጐናጨ በመሆኑ ከስብከት አንድ ጊዜም ዐርፎ አያውቅም ። መንገደኛ ስለነበር የቀናውን መንገድ አገኘና ሽል ማት ለማግኘት ከጣረ በኋላ ፡ በመጨረሻ ለላይኛው ፡ ጥሪ እሽ በጁ አለ ።"

በዚህ በጉዞው ላይ ፫ ዓመት ያህል እራሱን ለሐዋርያነት ሥራ ያዘጋጀበት ፣ ደግሞም ፪ ዓመት ያህል በቂሣርያና በሮም በእስር ቤት የቈየበት ፡ ከተፈታ በኋላ የሁለት ዓመት ሥራው

(፩) የመስቀል ያፍ የምትባለው በመጸው መጀመሪያ የምትታይ ያፍ ናት ። እርሱዋ ስትመጣ መጸው እንደገባ ይታወቃል ። በመስቀል በዓል ሰሞን በመታየቷ ሕዝቡ በሀገራችን (በኢትዮጵያ) የመስቀል ያፍ ብሎ ይጠራታል ።



ደግሞም ጥቂት ዓመታት ሁለተኛ በሮም የታሠረበት ተጨ ምረው ቢሆን ኑሮ የጳውሎስ የሐዋርያነት ሥራ ፴ ዓመት ተብሎ በተቈጠረ ነበር ። በጉዞውም ሥራዩ ብሎ የሚጐበኛቸው መዲና የሆኑትን ፡ ከዚህም ሌላ ትልልቅ ፡ በአፍላቸው የሚገኙትንና ንግድ የተስፋፋላቸውን ከተሞች ነበር ። ስለምን? ከእሊህ ጋር ትን ንሾቹ ከተሞችና መንደሮች ግንኙነት ስለአላቸው አዲሲቱ ሃይማ ኖት በቀላሉ ለእነዚህ ልትሰማ ይቻላል ።

በሰውነቱ ቍርጥማት (፩) በሽታ ቢኖርበትም ቅሉ ለውድ ድር የማይደክምና ለአደጋ የማይቻኮፍ ነበር ። ብዙ ዓመታት እየ ደጋገመ በደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ሰንደቅ ዐላማው የክርስቶስ መስ ቀል ስለሆነ ፡ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ኢሊሪኮ የክርስቶስን ወንጌል ሰብኮ ፈጸመ (ሮሜ ፲፭ ፡ ፲፱ ።)

በዚህ በቅዱስ ጳውሎስ በተደረገው የአዲስቱ ሃይማኖት ፍጥነት የወንጌል መዘርጋት እረዳት የሆኑት ለምሳሌ የግሪክ ቋንቋ በብዙ ሀገሮች ላይ ሠልጥኖ ስለነበር ፡ በአንድ ሮሜ መንግሥት ሀገሮቹ በመግዛታቸውና ቀደም ብሎ ዓለሙ በፈላስፎችና በሌ ሎች ሊቃውንት ተዘጋጅቶ ስለነበር ነው ። ነገር ግን ለሚያስደን ቀው ለጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥራ ዋናው ምክንያት ፈቃደ እግዚአ ብሔር ነው ካላልን በቀር የላይኛው ሐተታ በቂ ማስረጃ አይ ሆንንም ።

የአምላክ ፈቃድና ሌሎቹም ምክንያቶች እረዳት ቢሆኑትም ፍንክች የማይለውን ድፍረቱንና ጽኑ ተስፋውን ከማድነቅ ዝም አንልም ።

፩) ስለ ቅዱስ ጳውሎስ ጤንነት ጉዳይ የጥንቶቹና የዛሬዎቹ መንፈሳውያን መምህራን እንደሚደግፉት ቁርጥማት በሚለው የሰውነት በሽታ ገላ ፬ ፲፫ ካልእ ቆሮ ፲፪ ፯—፱ ካለመጠንቀቅ (ከጽዳት ጉድለት የተነሣ) አንድ በሽታ እንደ ወደቀበት ያሳያል ።

www.ethiopianorthodox.org

በገብዘው ለገጠሙት አደጋዎች የማይበገር ጉበዝ ፡ የደረሰበ ትን አደጋና ጭንቀት የሐሰት መምህራንን ምክንያት ስለአገኘ ወደ ቆሮንቶስ በጻፈት በሁለተኛይቱ መልእክቱ እራሱን ለማበላለጥ

ሲል ይቈጥረዋል ። እራሱን እየተከላከለና የቤተ ክር ስቲያን አገልጋይ በመሆኑ ከፍተኛነት እየተሰማው ምስጉን በሆነችመልእክቱ እንዲህ ይላል ። የክርስቶስ አገልጋይ ነን ቢሉ የኔማ ስንቱን እዘንጋው የለምን ? እጅግም ደከምሁ ብዙ ጊዜ ተገረፍሁ ብዙ ጊዜም ታሠርሁ ። ብዙ ጊዜም ለሞት ተዘጋጀሁ ።

አይሁድ አንዲት ሳትቀር አምስት ጊዜ ፴ ፱ ገረፉኝ ። ፫ ጊዜ በበትር ደበደቡኝ ። አንድ ጊዜ ድንጋይ ጣሉብኝ ። መርከቤ ፫ ጊዜ ተሰበረ ሌትና ቀን በጥልቅ ባሕር ውስጥ አደርሁ በየመንገዱም ሁልጊዜ መከራ እቀበል ነበር ።

በፈሳሽ ውኃ ተጨነቅሁ ፣ በወንበዴች ተጨነቅሁ ፣ በወገ ኖቼ ተጨነቅሁ ፡ በአሕዛብ ተጨነቅሁ ፣ በከተማ ተጨነቅሁ ፡ በዱር ተጨነቅሁ ፡ በባሕር ተጨነቅሁ ፣ በሐሰተኞች መምህራን ተጨነቅሁ ፡ በድካም ፡ በመከራ ፡ ከእንቅልፍ በመከልከል ፡ በመ ራብ በመጠማት ፡ በመራቆት ፡ ለምእመናን ሳስብ ከዚህም ሌላ ያገ ኘኝ መከራ ብዙ ነው ። ታሞ እኔ የማላዝንለት ማነው ? በድሎ እኔ የማልደነግጥለት ማነው ? መመከትስ የሚገባ ከሆነ እኔ በመከራዬ እመክለሁ (፩) ።

(፩) ካልእ ቆሮ ፲፩ ፳፫—፳፱



እንዲህ በሚገባ እውነትን በተመላ ኀሪት በውድድሩ መጨ ረሻ የደረሰበትን ጭንቅና መከራ ይጽፋል ። ከሁሉም ደግሞ አብልጦ የደከመውና ብዙ አደጋ የደረሰበት እውነት እንደ ትገለጽ በጣረ ጊዜ ነው ።

„ሊከራ የሚገባው ወታደር ችሎታ ያለው ቀስሉንና ጉዳ ቱን ቈጠረ "

ታሪክ ጸሐፊው ፓፓሪጎፑሎስ እነሆ እንዲህ ሲል በሰ ፈው ይጽፋል ። "ከዚያ ነበልባል ከሚወጣው ፡ ሲናገር ማር ጠብ ያለ የሚመስለው ! ግሪክን ከፊልጶስ ተገዥነት ለማላቀቅ ይጥር የነበረውን ዲሞስቴኒስን ትሰሙ አይመስላችሁምን ? ስለ ምን ? በዚያ በሰብሬዊ ላይ ሁለት መንፈሶች እፍ ብለውበ ታል ። መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ትክ ክል ናቸውና በወንጌል ትምህርት አንድ ለመሆን ይችላሉ ብሎ ያስተማረው ፤ የግሪክ መንፈስ እንደምን እንዲተረጉም ያስተ ማረውንም ትምህርት እንዴት እንዲያጸናው ያስተማረው "(፩) አደጋውን ብቻ በመጻፍ የቀመሰውን መሪር መዋረድ ሳያስታውሰው አያልፍም ። የደረሰበትንም መከራ የቻ ለው የአምላክ ማደሪያ ዕቃ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ፡ እራሱ በፈለሰፈው የአነጋገር ዘዴ ጭምር ነው ። እኔ ነፃ ስሆን ሲል በቀዳማዊ ቆሮንቶስ ይጽፋል እራሴን ለሁሉ አስገዛሁለሁና ብዙዎችን በሃይማኖት እንድ አደርጋቸው ዘንድ (፪)„

ይህም ማለት እኔ ከማንም ሥልጣን በታች ያይደለሁ የማንንም እርዳታ ፍላጎት የሌለኝ እራሴን ለሁሉ ገዢ አደርጌ ተገኘሁ ። ይህንንም ያደረግሁት እንደዋዘኛና እንደ እታላይ እነርሱን ደስ ለማሰኘት አይደለም ለብዙዎቹ የደኅንነትን በር እከፍትላቸው ዘንድ ነው እንጂ ።

፩) ፪) መጽሐፍ ገጽ ፶፩—፶፪
፪ ፱ ፲፱—፳፫

www.ethiopianorthodox.org

## ፩) የመጀመሪያው የቅዱስ ጳውሎስ ።
## ሐዋርያዊ ጉዞ ።

ይህ ጉዞ ከክርስቶስ በኋላ ከ፵፯-፵፱ ዓ/ም ስምንት ወሮች የፈጀነው ።

መጀመሪያ እንዳየነው ለሐዋርያነቱ ሥራ መነሻ ፡ የክርስቲያንነት መዲና የሆነችው የመጀመሪያዎቹ የግሪኮችና የአሕዛብ ከተማ የነበረችቱ ከተማ አንፆኪያ ናት ።

ከዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ከበርናባስና ከዮሐንስ (በኋላ ማርቆስ ተብሎ ከተሰየመው) ጋር ብዙ ፍሬ የተገኘበትን የመጀመሪያውን ጉዞ ጀመረ ።

በዚህም ጉዞ ቤተ ክርስቲያን የመሠረተበትን ቆጵሮስን እንዲሁም ከሳላሚስ እንዶሥቶ እስከ ጳፎስ ያሉትን ሀገሮችና የደቡብ ትንሽ እስያን ጳምፊልያን ፡ ጲስድያንና ሊቃኦንያን ጎበኘ ። ጳውሎስ ከረዳቶቹ ጋር በጳምፊልያ ከተማ በጴርጊያ ፡ በአንፆኪያ በጴስድያስ ከተማ ፡ በኢቆንዮም በልስጥራና በደርቤ ቤተ ክርስቲያናትን መሠረተ። በልስጥራም የሁለቱን ሐዋርያት ትምህርትና ተአምር ሰዎቹ እጅግ ስላደነቁላቸው «አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወረዱ»ሲሉ ተናገሩ ። ስለ ዚህም በርናባስን ድያ (፩) ጳውሎስንም ነገሩን የሚናገር እርሱ ስለነበር ሄርሜን (፪) አሏቸው ።

(፩) ድያ ሄርሜን የሚባሉትከጥንት የግሪኮች አማልክት ከ፲፪ቱ በኦሊቦስ (የግሪክ ፩ኛ ተራራ ፱ሺ ፱፻፲፯ ሜትር ከፍታ ያለው) ይኖሩ ነበር ተብሎ ከሚታሰቡት ናቸው ። የመጀመሪያውግ የሰዎችና የአማልክት አባትና ንጉሥ ነው ይሉታል ። የሰማይ ሥልጣን በእጁ የሆነ ደመናን ሰብስቦ ዝናም ያወርዳል ፡ ሲናገር ምድር ትናወጽ ነበር ይባላል ። ሁለተኛው የድያ ልጅ ነው ፈጣን በየብስና በአየር የሚበር የነጋዴዎች አምላክ ነው ። ደግሞም ነፍስን ወደ ሲኦል የሚያወርድ እሱ ነው ። ተብሎ ይታሰባል።

(፪) የሐ ሥራ ፲፬ ፲፪



## (፪) ሐዋርያዊ ጉዞ ።

ይህ ጉዞ ፫ ዓመታት ያህል የፈጀ (፵፱ - ፶፪) የመጀመሪያይቱ የአውሮፓ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት በመሆኑ በመቄዶንያ ከተማ በትልቁ ስዩስ በዓለም ታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ በየጊዜው ይተረክል ። በዚሁም አብረው ያገለግሉ የነበሩትን ሲላስንና ጢሞቴዎስን አስከትሎ ከዚህ ቀድሞ በሶርያና በቂልቅያ የመሠረታቸውን ቤተ ክርስቲያኖች አጸና ።

ከዚያም አልፎ በትንሽ ፍርጊያንና በትንሽ እስያ በአለችው ሀገር በገላትያ ቤተ ክርስቲያን ከመሠረተ በኋላ ወደ ጥሮአዳ ወረደ እዚህም ሳለ መቄዶንያን ይጎበኝ ዘንድ በራዕይ ስለተገለጠለት በሳምትራቂስና በኒያጶሊስ በኩል አድርጎ ፊልጶስዩስ መጣ ። ከዚያም የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን መሠረት ወደ ጣለበት ተሰሎንቄና ቤሪያ መጣ ። አያይዞም አቴን ከጥቂት ጊዜም በኋላ ቆሮንቶስ (፩) ከቆሮንቶስም በመርከብ ወደ ኤፌሶን ከዚያም በቂሣርያ አድርጎ የጳለስቲን ዋና ከተማ በሆነችው በኢየሩሳሌም በኩል ወደ አንፆኪያ ተመለሰ ።

## ፫ኛው ሐዋርያዊ ጉዞ ።

ይህ ጉዞ ከ፬ ዓመቶች ይበልጥ የፈጀ ነው (፶፫ - ፶፰) ። የቀድሞው ምኞቱ የዓለም መናገሻ ከተማ ሁና የነበረችውን ሮምን ለመጎብኘትና የሐዋርያነቱን ሥራ በዚያ ለመቀጠል የተመኘው ስለተፈጸመለት ይህ ጉዞው ዝና ያለው ነው ። በዚህም ጉዞ የገላትያንና የፍርግያን ቤተ ክርስቲያኖች ጎበኘና ወደ ኤፌሶን መጥቶ በዚያ ፪ ዓመት ከ፫ወር እንደ ሰረፍት ኖረ ።

(፩) ደራሲው ስለመቄዶንያ አቴንና ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በተለየ ክፍል በዚሁ መጽሐፍ ወደ ፊት ስለሚገልጽ ሐተታ ሳይጨምር ያልፋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከኤፌሶንም የመቄዶንያንና የአካይያን (የግሪክን) ቤተ ክርስቲያኖች ከጐበኘ በኋላ አያይዞም በጥሮአስ፡ በአሶ፡ በሚጢሊኒ፡ በኮስ ፤ በሚሊጦን ፡ በጢሮስ ፡ በጵቶልማይስ ፡ በጳለስቲን ፡ በአለችው በቂሣርያ አድርጎ ኢየሩሳሌም ደረሰ ።

እዚያም "ኦሪትንም ይህንንም ቦታ የሚያመልክ ብለው፡ስለወነጀሉት ሊገሉት እጃቸውን ዘረጉበት ። የሮማውያን ወታደሮች ከተነሣበት ሕዝብ አድነው በወታደር እንደተከበበ የጳለስቲን ገዥ ወደሆነው በቂሣርያ ወደ ሚኖረው ሮማዊ ቀረበ ምክንያቱም የሮም" ዜጋ (ሮማዊ) ነኝ ስላለ ነው ። ፪ ዓመት በቂሣርያ ከታሠረ በኋላ ደግሞ ሮማዊ ነኝ አለ ። ይኸውም የቂሣርያው ሮማዊ ገዥ ለአይሁድ ንጉሥ ለሄሮድስ አግሪጳ ፪ኛ ከሰጠው በኋላ ኢየሩሳሌም በአለው በአይሁድ ፍርድ ቤት ነገሩ እንዲታይ ለመላክ በማሰቡ ከዚህ ፍርድ ለመራቅ ሲል ነው ። ከዚህ በኋላ ሮማዊው ገዥ ፪ ዓመት በእሥር ቤት ወደሚቈይበት ወደ ሮም ለመላክ ተገደደ ።

ወደሮምም በሚዲቴራኒያንና በአድሪያቲ ባሕር ላይ ሲጓዝ ጭንቅ የተመላ ነበር ። የሚሔድበት መርከብ ሚራ በሚባል ቦታ ተሰበረ ። ከዚያም በሌላ መርከብ ወደ ሲራኩስ ፤ እዚያም ፫ ቀን ከቈየ በኋላ ወደ ሬጊዮን መጣ በኋላም ጰቲዮል ከዚያም ሮም ደረሰ ። በባሕር የደረሰባቸውንም ጭንቀት ወንጌላዊው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ከ፳፯ - ፳፰ በአሉት ምዕራፎች ይጽፋል ። ጳውሎስ ሮም ከመምጣቱ ቀድሞ ወንጌልን በሰፊው በዓለም ለመዘርጋት ይመኝ የነበረው ተፈጸመለት ። ስለምን? የሁለት ዓመት እሥር በነበረበት ጊዜ ዘበኞቹ ይቈጣጠሩትና ይከ



ለከሉት ስለነበረ ፡ ከዚያ በነበሩት ክርስቲያኖች እየተረዳ የሐዋርያነቱን ሥራ እንደሚገባ ይቀጥል ነበር ።

ከላይ የዘረዘርናቸው ፫ቱ የጳውሎስ ጉዞዎች በሐዋርያት ሥራ በሰፊው ተተርከዋል ።

፲፬ ፩–፳፯ ።

## ፬ኛው ሐዋርያዊ ጉዞ ።

፬ ዓመት በሮም ከታሠረ በኋላ ነጻ ተለቀቀና የመጨረሻውን ፬ኛ ሐዋርያዊ ጉዞ አደረገ ። እስጳንያ ደርሶ መቄዶንያንና እስያን ከጐበኘ በኋላ በኤፌሶን ጢሞቴዎስን ፤ በቀርጤስ ቲቶን ኤጲስቆጶሳት ሹሞ አስቀመጣቸው ።

ዳግመኛም ሮምን ከጐበኘ በኋላ ከሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በኔሮን ዘመን በ፷፯ ዓመት የሰማዕትነትን ሞት ተቀበለ ።

ይህ ጉዞው ለመደረጉ የወሬ ምንጭ የሚሆኑን ፤ መልእክቶቹና የጥንት የአበው ታሪክ ነው ። ስለምን ? የቅዱስ ጳውሎስ ሕይወት ታሪክና ጉዞ ጸሐፊ ወንጌላዊው ሉቃስ በሮም በሁለት ዓመት እሥሩ ስለአቆመ እስከ መጨረሻው ባለመጻፉ ነው ።

በእርግጡ ቅዱስ ጳውሎስ በ፬ኛው ጉዞ እሊህን ቦታዎች እንደጐበኘ እራሱ እንዲህ ይላል ። "ነገሬን በዚህ መጽሐፍ ፈጽሜአለሁ ከብዙ ቀን ጀምሮ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ እወድ ነበርና ወደ እስጳንያም ስሔድ እግረ መንገዴን አያችሁ ዘንድ ተስፋ አለኝ ። (፩)

፩) ሮሜ ፲፭ ፳፫—፳፱

www.ethiopianorthodox.org

በዚህች ፬ቱን የጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞዎች በአጭሩ የምትገልጽ ጽሑፍ ላይ አንባቢ ዓይኑን ጣል ቢያደርግ በእንዴት ያለ ትጋትና ፍጥነት ከመልካም ቅናት ጋር ደግሞም በቅን ስሜት ፈጽሞ የወንጌል ስብከት በዓለም ላይ እንደተዘረጋ ይረዳዋል ።

## ሁለተኛ ክፍል ።

## ቅዱስ ጳውሎስ በግሪክ ሀገር ።

ፊልጵስዩስ ተሰሎንቄ ፤ ቤሪያ አቴን ቆሮንቶስ

አሁን ቅዱስ ጳውሎስ በእስክንድርያ - ጥሮአስ ከጥንቱ ቦታ ምን ያህልም በአልራቀችው ትልቅ ወደብ በአላት የባሕር ዳር ከተማ ይገኛል ።

ከዚህ ቀደም ብለን እንደተናገርነው ቅዱስ ጳውሎስ ከኤውሮፓ ሀገሮች ወደ አንዷቱ ወደ ግሪክ ይሻገር ዘንድ የአምላክን ትእዛዝ በዚሁ ሳለ ተቀበለ ። ለጳውሎስ በሌሊት አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ በማለት ወንጌላዊው ሉቃስ ታሪኩን ይቀጥላል ። ወደ መቄዶንያ እለፍና እርዳን እያለ ሲለምነው ራዕይ ተገለጸለት ” ።

ኤውሮፓ ገና በአምልኮተ ጣዖት ጨለማ የምትገኘው ከዚህ ቀድሞ እስያ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሰማች እርሱዋም መስማት ይገባታል ።

### (፩) ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ።

ከጥሮአስ ጳውሎስ በ፶፩ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከረዳቶቹ ከሉቃስ፥ ከሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር በሳምትራቱ አድርጎ ኒያጶሊስ (ዛሬ ካቫላ የምትባለው) የፊልጵስዩስ የባሕር ወደብ



በነበረችው ከመርከቡ ወረደ ። ከዚያም ወደ ፊልጵስዩስ መጣ ። ያን ጊዜ ፊልጵስዩስ በአፍላዋ ላይ ያለች በመሆኑዋ ልትታይ የተገባት ከተማ ነበረች ። እስከ ፲፰ኛው መቶ አፍላዋ አልጠፋም ነበር ። ዛሬም የቀድሞው እርዝራዥ (ፍራሹ) ይታያል ።

በዚች ከተማ ሐዋርያው በኤውሮፓ በግሪክ ምድር የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ቻለ ።

ይህንንም ሐዋርያዊ ተግባር ሲፈጽም ከአይሁድ ብዙ መሰናክል ሲደርስበት ያንን ያህል ደግሞ ፍጻሜው በከተማው አለቆች ተይዞ መደብደብና መታሠር የሆነ ፤ ከጣዖት አምላኪዎች ደረሰበት ።

የመጀመሪያይቱ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን አዲሲቱን ሃይማኖት በመቀበል አባል የሆኑ ፤ ከቲያጥራም ፤ ከትንሽ እስያ ከተማ የምትሆን ልዲያ የሚልዋት አንዲት ቀይ ሐር ሻጭ ሴት ከቤቶቿ ጋርና የእሥር ቤት ጠባቂው ከነ ቤተ ሰቡ ናቸው ።

ቅዱስ ጳውሎስ አዲሲቱ ሃይማኖት በፊልጵስዩስ ከፍ ከፍ በማለቷ ፤ የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ጽድቅን ወዳጆችና እግዚአብሔርን ፈሪዎች በመሆናቸው ደስ ብሎት በኋላ ለሌሎች ክርስቲያኖች ምሳሌ ይሆን ዘንድ እንደጻፈው፥ የትምህርቱ ፍሬ በመልካም መሬት ላይ እንደወደቀ ያሳያል ።

የፊልጵስዩስ ሰዎች ጳውሎስ ያስተማራቸውን የወንጌል ቃል ተጠንቅቀው ይዘው ገንዘብ እያዋጡ ለሥራው መከሔጃ እርዳታ ይልኩለት ነበር። ጳውሎስም በበኩሉ የሚጠነቀቅላቸው በብዙ ነበር ። ስለዚህ ፫ ጊዜ ይህችን ቤተ ክርስቲያን እራሱ ጎበኛት። ሌላም ጊዜ ይህች ቤተ ክርስቲያን እርምጃዋ እያደር እንዲቀጥል የእሱ ተከታዮች ከሚሆኑት ረዳቶቹ ወደ ፊልጵስዩስ ላከ ። እጅግ ከፍ አድርጎ የፊልጵስዩስን ሰዎች ይወዳ

www.ethiopianorthodox.org

ቸው እንደ ነበር የሚያመለክተው ወደ እነሱው በጻፉት መልእክቱ «የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ ልጆቼ ፍቅሩና ጸጋው ከእናንተ ጋር ይሁን በማለቱ ያስረዳል ።

ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ተቀምጦበቸው የነበሩት ቦታዎች በኋላ ዘመን እየተቈፈሩ ቢመረመሩ ቅዱስ ቦታዎች ሁነው ተገኙ ። ማለት ለምሳሌ ታሥሮበት በነበረው ቦታ ቢቈፈር ትንሽ ቤተ መቅደስ ተገኘ ። ደግሞም «ጸሎት ወደ ሚደረግበት ስፍራ ወደ ወንዙ አጠገብ ወጣን» እንደሚለው በሐዋርያት ሥራ ፣ በዚህም ቢቈፈር የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ቤተ መቅደስ ተገኘ ።

ደግሞም አንድ በሰብላ በረድ በ፫ኛው መቶ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በቅዱስ ጳውሎስ ስም የታነፀ ቤተ መቅደስ ከብዙ ድንጋይ ጽሑፎች ጋር ተገኘ ።

## ፪) ጳውሎስ በተሰሎንቄ ።

ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ዋና ከተማ የአቴና ተከታይ (ሁለተኛ) የሆነችው ሊነገር የተገባው ታሪኳ የሚጀምረው ክርስቲያንነት ከመጣ ወዲህ ነው ። በመካከለኛው ዘመን ለሰሜን ግሪክ ሕዝብ ከጠላት መሸሸጊያ ምሽግ ነበረች ።

ከ፶፩—፶፪ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በአፍላዋ ላይ ሳለች የመድኅነ ዓለምን ቃል ፤ መንፈስ ቅዱስን ከተመላ ከጳውሎስ ሰማች ። በዚህ ጊዜ የተሰሎንቄ አይሁድ የመቃወም ውጊት ጳውሎስን ገጠሙት ። በእርሱዋም መጀመሪያ የወንጌል ቃል ተሰብኮ ክርስቲያንነት ወደ ኤውሮፕ ስለገባ «መልካም በር ተባለች ።»



ቅዱስ ጳውሎስ በጐበኛት ጊዜ ይህች የመቄዶንያ ዋና ከተማ የጥንቶቹን አምላኮች ስታመልክና አምልኮቷንም በየዓይነቱ በውድድርና በሌላም ደስ በሚያሰኝ ነገር ስትገልጽ አገኛት ። ጥቂቶች ብቻ ትምህርቱን ሲቀበሉ ፡ ሌሎቹ ከትልልቅ ቤተ ሰብ ተወላጆ የሆኑት ወንዶችና ሴቶች ፈጽመው በጣዖቱ ያመኑ ስለሆነ ፡ የሚያስተምረውን ትምህርት ፍሬ እንዳለው አልቈጠሩትም ።

አይሁድ ጳውሎስ በግሪኮች መካከል እየተከበረ ትምህርቱ እንደ ተሰማለት በባዩ ጊዜ የሃይማኖት ወገኖቻቸውን ሰብስበው ሽብር ስለአስነሡ በመላይቱ በተሰሎንቄ ታላቅ ብጥብጥ ሆነ ። በዚህም ምክንያት ወደ ቤሪያ የግሪክ ከተማ ወደ ሆነችው እንዲሔድ ተገደደ ።

ምንም አይሁድ ያን ያህል ቀንተው ትምህርቱ ፍሬ የሌለው ሁኖ እንዲቀር ተንኰል ቢሠሩ ፤ የተሰሎንቄ ሰዎች ወንጌልን እንዲቀበሉ እውነት ስለመራቸው ፤ ለመላው ለመቄዶንያና ለአካይያ (ለቀረው ግሪክ ማለት ነው) ቈይተው አስተማሪ ለመሆን በቁ ።

ከነሱም ብዙዎቹ በሮማውያን ነገሥታት በሆነው በትልቁ ስደት የሰማዕትነትን ሞት መቀበላቸው አልቀረም ። ከእሊሁም አንዱ አሚሙቱ ቅድስና ያለው የተሰሎንቄ ከተማ ጠባቂ (፩) ቅዱስ ዲሚጥርዮስ ነው ።

(፩) በግሪክ ሀገር አንድ ልማድ አለ ። ይኸውም አንዱን ታቦት ለይቶ ለከተማ ወይም ለመንደር ቍጥሩ ከፍ ያለ ሕዝብ ለሚኖርበት ፤ ጠባቂ ማድረግ ነው ። ይህም ሲሆን ታቦቱ በሥራ ወይም በሞት ታሪኩ ከቦታው ጋር የተያያዘ ሲሆን ነው ። ወደፊት እንደምናየው ይህ በክርስቲያንነት ዘመን ብቻ ሳይሆን በዘመነ ጣዖትም ይደረግ ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ምክንያት በሐዋርያት ዘመን የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን የአማኞቹ ማኅበር በያለበት የተመሠረተው ተስፋፋ ። ይኸውም የአዲሲቱ ሃይማኖት የኑሮ ብርሃን የሚፈልቅበት ምድጃ ሆነ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ዋና ከተማ ሁና ግሪኮችን የክርስቲያኖች ጠላት እንዳይጠቃቸው መከላከያ ጠንካራ ግንብ ሁናቸዋለች ።

ከዚህ ወዲያ የትልቁ ሐዋርያ ጳውሎስ ቅዱስ ተግባር የቱን ያህል እየተስፋፋ እንደሔደ ለመረዳት የሚያዳግት አይደለም ።

## (፫) ጳውሎስ በቤሪያ ።

በተሰሎንቄ ያሉትን ወንድሞቹን ከተሰናበተና የመጨረሻ ንግግሩን ከደረገላቸው በኋላ ፤ በ፶፩ኛ ዓመት መጀመሪያ ከክርስቶስ በኋላ በሌሊት ከዚያ ወደ ቤሪያ ሔደ ። በጉዞውም አብረው የሚከተሉት በመልእክቱ ወታደሮቹ ከሚላቸው ሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር ፲፪ ሰዓት ከተጓዘ በኋላ ከቤሪያ ደረሰ ።

ቤሪያ «የጥንት ከተማ ዝና ያላት» ጳውሎስ በሔደ ጊዜ ተስፋፍታና ተሟሙቃ በክብር ላይ ነበረች ። በዚህ ጥቂት ቀኖች ከአስተማረ በኋላ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች መሠረተ ። በቅዱስ ጳውሎስ ፤ ክርስቲያንነት የተሰበከበት የጥንት ደረጃ እስከ ዘመናችን ድረስ ይታያል ። ይህም «የቅዱስ ጳውሎስ ደረጃ» በመባል የታወቀ ነው ።

በዚሁ ሥፍራ ስለፍሬያማ ስብከቱ መታሰቢያ በየዓመቱ በሚደረገው ክብረ በዓል ታላቅ ጸሎት ይደረስበታል ።

DN Solomon Yohannes



ብዙ ቀኖች ያይደለ እንደተቀመጠ በተሰሎንቄ ያሉ ቀናተኞች አይሁድ ለመቸውም የማይተኙለት ጠላቶቹ፤ በቤሪያ ትምህርቱ እንደተሰማለት በሰሙ ጊዜ ሕዝቡን ሊያውኩና ሊያስነሡ እየተፋጠኑ ወደዚያ ስለመጡ ቤሪያን ጥሎ ለመሔድ ተገደደ ።

እንግዲህ መቄዶንያን መልቀቁ ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ የሐዋርያነቱ ሥራ በእጅጉ ስላደከመው በተለየ እንደ አንድ ነገር ጠልተውት ያስጨንቁት ከነበሩ ጠላቶቹ ይላቀቅ ዘንድ ዕረፍትን ፈለገ ።

በእንዴት ያለ አኳኋን ያሳድዱት እንደነበር ለማመልከት ወደ ፊልጵስዩስ በጻፋት መልእክቱ በውሻ መስሏቸዋል ፫ ፪ ።

የጠላቶቹን ጥልና ጭቅጭቅ ወደማይሰማበት ቦታ ለመሔድ ቍርጥ አሳብ አደረገ ። ይህም አዲስ የወንጌል ስብከት ፕሮግራም ግሪክን ፤ በተለየም አቴንን ለመጐብኘት ነው ።

## (፬) ጳውሎስ በአቴን ።

ጳውሎስ ወደአቴን በባሕር ላይ ጉዞውን ጀመረ ። ወደ ሜቲኒስ የጥንት የቤሪያ ባሕር ወደብ ኤሌብቴሮሆሮስ ወደ ሚባለው ከመጣ በኋላ ከመርከብ ገብና በኤጊዎን ባሕር ላይ በተሰሎንቄ ዳር እያደረገ ኤብሪፖስ የሚባለውን ጠባብ ከአለፈ ወዲያ በመጨረሻ ከ፫ - ፬ ቀን ከተጓዘ በኋላ አቴን ደረሰ ።

ከመውረዱ በፊት ገና ከሩቅ የአቴና (፩) መንታ ጦር ጫፉ ከወርቅ የሆነ ሲያንጸበርቅ አየ ። ከመልከሚቱ ከተማ ዳር ከሆነ

፩| አቴና የምትባለው ሴት አምላክ ፤ የአቴን ከተማ ጠባቂ ነበረች ። በፊት እንደተባለው የጥበብ አምላክ በመሆኗ አቴናውያን ጥበብን ወዳጆች ስለነበሩ በተለይ ያመልኳት ነበር ። አክሮጶሊስ ከሚባለው ኮረብታ ላይ አንድ ያማረ ቤተ መቅደስ ነበራት ። በዚሁ ጫፍ ጦር እንደያዘች የመላ ሰውነት ሐውልት ነበራት ። ይኸውም እስከ ባሕሩ ድረስ ይታይ ነበር ይባላል ። ሐውልቱ ብቻ ሲጠፋ መቅደሱ ከማማሩ ጋር ዛሬም ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

ፓላስ ከሚሉት ቦታ ዐረፈና ቀኖቹን ሙሉ አዲሱን ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ማናቸውንም ነገር ለመረዳት ከተማይቱን ሲዘር ይውል ጀመር ። አቴን የጥንት የግሪክ ሥልጣኔ የታየበት የዕ ውቀትና የጥበብ መዲና የነበረችቱ ፡ አእምሮው በዕውቀት የተ መላ ሐዋርያ ጳውሎስን ቸል ቸል ለማለት አልናቀችውም ።

እርግጥ ነው በዚያ ጊዜ የፋርስን መንግሥት (፩) አቸንፋ በክብር ላይ ክብርን የጨመረችና የፔርክሊስ ጊዜ ፪ ግሪክ አይደለችም ። ቢሆንም የቀድሞው ክብሩዋ ፈጽሞ ስለአልጠፋ ርዝራዥ ይታይ ነበር ጳውሎስ በመጣበት ዘመን አቴን ከዓ ለም ዕውቀትንና ጥበብን ለመገብየት የሚሰበሰቡባት አደባባይ ነበ ረች ። በዚያ ጊዜ ዝናቸው በየትም የተሰማ ትምህርት ቤቶች እስከ ዛሬም የሚደነቁ ስለነበሩት በሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ከምሥራቅ ከምዕራብ እየመጡ ይጐበኙዋት ነበር ዛሬእንኳን የቀድሞው ታሪ ካዊ ተግባሮች ፈራርሰው ሳለ የጥንቱን ክብር አጉልተው የሚ ያሳዩ መግረያዎች ትንሽ አይደሉም ።

በዚያን ዘመን አቴን ከመላይቱ ግሪክጋር ቆሮንቶስ በ፻፵፮ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሮማውያን እጅ ከወደቀች በኋላ ,,ሄሊኖሮማይክሳ,, ከሚባለው ዘመን ደርሳ ነበር ።

(፩) ጳውሎስ የጥንት ሃይማኖት ዓይነቶች ከተከማቹበት ከተማ ግሪክ ከ፫ ጊዜ ይበልጥ የያኔውን ትልቁን የፋርስ መንግሥት በ፶ኛው መቶ ደጋግማ በማቸነ ፍዋ ዝናዋ በዓለም ተናኝቶ ነበር ።

(፪) በፔሪክሊስ ጊዜ ከማናቸውም ዘመን ይልቅ በሥልጣኔ ከፍ ያለች በች በመሆኑ ክብርዋንና ዝናዋ ምድር ጠበች ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org



በትልቁ ሮም መንግሥት ዘመን ግሪክ ከሮም ግዛት አን ዲቱ ሁና አካይያ እየተባለች ትጠራ ነበር ። እርሱዋም በመ ግዛት ላይ ሳለች የዓለሙ መድኀን በይሁዳ ተወለደ ። ይህ የሰ ውን ልጅ በተስፋ ከፍ የሚያደርገው መልካም ዜና ለአቴን ሳይታወቅ አለፈ ። ብቻ ከልደት በኋላ ፶ ዓመት ያውም ሲበ ልጥ መንፈስ እግዚአብሔር የመላበት ጳውሎስ ለአቴናውያን አዲሱን የደኅንነት ዜና አመጣላቸው ።

ጳውሎስ የጥንት ሃይማኖት ዓይነቶች ከተከማቹበት ከተማ ተገኝቶ የጥንቲቱን አቴን ትልቅነቷንና ክብሯን የሚገልጡ ሕን ፃዎችንና ልዩ ልዩ ሥራዎችን የተረፉትም እስከ ዛሬ የሚ ታዩትን ይጐበኝ ጀመር ። ስለምን ? በዚያ ዘመን አቴን (፩) አፍላዋ ገና አልጠፋም ነበር ። ፓርቲኖንና የአቴና ግሩም ሐውልቶች እንዳሉ ሁነው እንደ ብርሃን ተግ ተግ እያሉ ይታዩ ነበር ። ሐውልቶች ፤ መሠዊያዎችና ሌላም ጥቃቅን ለስዕለት የሚገቡ ዕቃዎች ለአቅርጶሊስ ተጨማሪ ጌጥ ነበሩ ። ሌሎችም ክብር ያላቸው ከተማይቱን ያስጌጡ ነበሩ ። እሊህ ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ የቀድሞዪቱን ግሪክ ፡ ትልልቆቹን ፈላስፋዎች ፤ ሰባ ኪዎቹን ፤ ሊቃውንቶቹን ፡ የፖለቲክ ሰዎችንና ጥበብ ዐዋቂ ዎችን በጠቅላላው እሊያን ሁሉ የቀድሞ ሥልጣኔ ፈጣሪዎ ችን እንዲያስብና እንዲያደንቅ በቂ ማስረጃ ሆነውታል ።

ከተማይቱን እየዞረ ሲጐበኝ ስቅራጥስን ወይም ፕላቶንን አላገኘም አካዲሚያውን ግን አየ (፪) ። በእርግጥ እንደ ሙብረቅ የሚያስገመግመውን የፔሪክሊስን ድምጽ አልሰማም

(፩) አቴናና አቴን ልዩነት ስላአለባቸው አንባቢ እንዲያስተውል ማስታወሻ ይሁነው ። አቴና ሲል ጣዖቲቱን አቴን ሲል ከተማዪቱን ያመለክታል ። (፪) ፕላ ቶን ያስተምርበት የነበረው የፍልስፍና ትምህርት ቤት ።

ያንንም ደግሞ እንደ አንበሳ የተቈጣ የሚመስለውን ዲሞስቴ ኒስን ግን ሊዳንቅ ያላቸውን የተናገሩባትን ቦታ አየ ። ፊዲያስን ወይም ኢቅጢኖስን ወይም ካሊክራቴን አላገኘም ። ግን ለዘለዓለም የማይጠፋውን የእጃቸውን ሥራ አየ ። ምንም እንኳን የቀድሞውን የአቴንን ክብር የሚገልጡትን ሁሉ ቢመለከት፥ "በከተማይቱ ብዙ ጣዖታት ሲመለኩ በየ ጊዜ ሰውነቱ ተበሳጨበት ,, ይህም ማለት ከተማይቱ በሃይማኖት ረገድ በንደዚህ ያለ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመገኘቷ ነፍሱ እስከ መጨነቅ አዘነች ማለት ነው ። በጣዖታት መቅደሶች ፤ በመሠዊያዎችና በጣዖታት ተመልቷ በየ ጊዜ ደግሞም አቴናውያን ተንቀሳቃሽነት የሌላቸውን ጣዖታት በተለየም እንግዶች አማልክት የተባሉትን በሙሉ ልባቸው ሲያመልኩ በየ ጊዜ እጅግ አዘነ ።

የቅዱስ ጳውሎስም ከሐዋርያት ከፍተኛ የሆነው የወንጌል ትምህርቱ በተሰማ ጊዜ የሃይማኖት ጭቅጭቅና ክርክር እየ ባሰ ሔደ ።

በዚያ ዘመን የነበሩት ፈላስፎች አዲሾቹ ፒታጎራውያንና ፒላቶናውያን የቀድሞውን የግሪክ ሃይማኖት ለማጽደቅ በከንቱ ደከሙ ። የሃይማኖታቸውም ዋና መሠረትና የሕዝቡን መንፈስ የሚቀሰቅስ ሚቶሎጊ (ውሸት ታሪክ) ነው ብለው ፈላስፎቹ የጻኑበት የአባቶችን ሃይማኖት ለማቈየት ለሕዝቡ ፈጽሞ እንግዳ ሆነ ። ከዚህ ሌላ በቀድሞው ሃይማኖት ሕዝቡ



በመንፈሱ የሚሠርዕበት ሌላ ነገር አላገኙም ። ሕዝቡም አሻፈረኝ በማለት ዝም ብሎ የወደደውን ብዙ አማልክቶችና የቤቱን ጣዖት (፩) ያመልክና በልማድ ሃይማኖትና በርኩሳት መናፍስት (ከሃይማኖት ሳይቀላቀል) ጸና ።

ፍልስፍና በምሥራቅ በተስፋፋ ጊዜ ከዚያ ብዙ አማልክት ተጨመሩና የያይነቱ ሃይማኖት በዛ ። ቅጥ በሌለው አኳኋን የሚመለኩ እንግዳና መስሐቲ የሆኑ የፋርስና የግብጽ አማልክትን ማምለክ ስለጀመሩ ፤ በዚህ የሕዝቡ ልብ በሃይማኖት ብቻ አልተሳበም ጥፋት በመላበት ጉዳና መንግዝም ጀመረ እንጂ ።

በዚህም ድብልቅልቅ መካከል ሕዝቡ ምናልባት በሃይማኖት ረገድ ደስ የተሰኘ መስሎት ፤ አዲስ ያልታወቀ አምላክ ያበጁለት ዘንድ ጠየቀ ። በእንግዶቹም አማልክት መሠዊያ ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ያለበት ተጽፎላቸው ነበር ። ለእስያ ፤ ለኤውሮፓና ለአፍሪቃ አምላኮች ለዐልታወቁና ‹ለእንግዶች አማልክት› ኢየሮኒሞስ (፬፻፳) የሚባለው ላቲናዊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንደጻፈው ።

(፩) በቀድሞ ዘመን ጣዖት ግሪኮች ዛሬ በኛ ሀገር በየባላገሩ አድባር እንደሚባለው ፤ በየቤታቸው በአጥር ግቢ ውስጥ አንድ ከድንጋይ የተቀረፀ ጣዖት ነበራቸው ። በዚህም የቤተ ሰብ በዓል ሲሆን መሥዋዕት ይሠዉ በቃል ይኸውም የቤት አምላክ ይባል ነበር ። ክርስቲያንነት ከተሰበከ በኋላ በጭራሽ ስላጠፋው ዛሬ አይገኝም ። እንግዲህ ይህ በሀገራችን የሚደረገው የጥንት ጣዖት አምላኪዎች ያደርጉት የነበር ፤ ከክርስቲያን ሕግ የወጣ ጣዖት ማምለክ መሆኑ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

"ለዐልታወቀ አምላክም (፩) የሚለው ጽሑፍ ያለበት ፡ መሠዊያ ጳውሎስ በአቴን ክብር ኑሮዋቸው ከአያቸው ሁሉ ፤ ይበልጡን ስሜቱ ተሰብስቦ የወደቀበትና በአድንቆት ዓይኑ ልቡ ናው ያረፈበት እዚህ ላይ ነው ። ቄይቶም እንደምናየው ለአቴ ናውያን በአርዮስ ፋጎስ በተናገረው ቃል አርእስት አድርጎት እናገኛለን ።

ቅዱስ ጳውሎስ ሲዘዋወር በተመለከተው ድንቅ አስተያየት ከተመላ በኋላ የአዲሲቱን ትምህርት ስብከት እንደተለመደው መጀመሪያ በምኩራብት አማኞቹ ለማክበር (፩) በሚሰበሰቡበት እየሔደ አስተማረ ። በኋላም በገበያ (፪) የማንም ሃይማኖት ወገን ቢሆን ለአገኘው ሁሉ ያስተምር ጀመር ።

እንደ ሶቅራጥስ በማስተማር ዓይነት የሃይማኖት ክርክር ሲደ ረግ ፤ በድንገት በአቴን ሕዝብ መካከል ሁሉ እንግዳ መስሎ በሚታየውና በተለየም በኤስጦኮችና በኤጴቄሮስ ፈላስፎች መከ ከል ሽብር ተነሣ ።

---

፩) ፤ እርግጠኛው የዚህ መሠዊያ ጽሑፍ እስከ ዛሬ ድረስ ምድርን እየቈ ፈሩ በሚመረምሩ (አርኪዎሎጊስትስ) አልተ ገኘም ። በ፱ተኛው መቶ ከክርስቶስ በኋላ የነበር ዲዮኦኒሱ ላየትሪዮስ የሚባል የግሪክ ደራሲ እንደሚነግረን ፫በአቴን ከተማ ዳርና እንዲሁም በሌሎች ከተሞች ያልተጻፈባቸውን መሠዊያዎችን ነው ለዐልታወቁ አማልክት የሚሏቸው ። እንደ ፓብ ሳኒያንስ ደግሞ ከጳውሎስ በኋላ ፶ ዓመት የተቀመጠ ተዘዋዋሪ (ቱሪስት) በተለየም አቴና ተቀማጭ የነበር ፤ ለዐልታወቁ አማልክት የተሰጡት መሠዊያዎች የታነጹት ከፋሊሮ እስከ አቴን በሚወስደው መን ገድ ግራና ቀኝ ነበር ይለናል ።

(፪) ያልታወቁ አምላኮችና አርበኞች ተብለው የተሠየሙት አማልክት መሠዊያ ዎች ነበሩ ። እንዲሁም ደግሞ በኦሊጊያ ነው ተብሎ ተገምቷል ። የዛሬዎቹም ሊቆች ያለመሠዊያ በእርግጥ እንደነበር ያምናሉ በአልታወቀው አምሳክ የሚደረገው መሐላ እረ ባልታወቀው ነበር ።



ይበልጡንም እነዚህ ሁለቱ የፈላስፎች ወገኖች ቅዱስ ሉቃስ ያስታወሳቸው ፡ በዚያ ዘመን ዕውቀት አነስ ያለበት ሲሆን ፡ ከሌሎች ፈላስፎች ሁሉ ትምህርታቸውን አስፋፍተው በሕዝቡ ላይ ስለናኙትና ሞገስ አግኝተው ስለ ነበር ነው ።

ኤጴቄሮሶች ስለሃይማኖት ጉዳይ ፊጅ የሆኑት አምላኮች ስለሰዎች ዕድል አሳባቸው ምን እንደሆነ ዐይታወቅም ብለው በማስተማር ፤ ስለነፍስ ሕያውነት ፤ ናትም አይደለችም ብለው መልስ ሊሰጡ አልወደዱም ።

እስጦኢኮች ብዙ ከኤጴቄሮሶች የሚለዩ እንዲህ በሚ ለው ነበር ትምህርታቸው ። ሰው የመከራው ጌታ መሆን ይገባ ዋል ። በሕይወቱ ከሚመጣበት ፈተና ሁሉ አንዳች ጕዳት እንዳያገኘውና ደስታም ኃዘንም የበላይ አዛዥ እንዳይሆኑ ። ስለምን ? ኀዘንና ጕዳት ያንን ያህል ክፉ አይደሉም ። ደስ ታም ሁል ጊዜ መልካም አይደለም ።

አዲሲቱ የጳውሎስ ትምህርት ስለእርሱዋ በገበያ ከኤጴ ቄሮሶችና ከእስጦኤኮች የተነጋገረውና የተከራከረው ልዩ ምሥጢር ያለው ሁኖ ታየ ። በዚህም ጊዜ ግማሾቹ ይህ ለፍ ላፊ እያሉ አቃለሉት ሌሎች ደግሞ በበኩላቸው አዲስ አማ ልክትን (፩) ያስተምራል አሉ ።

---

(፩) የሚሰበሰቡት የአይሁድን ሃይማኖት ለማክበር ግሪኮች ነበሩ ። ቈይቱ ውም ጣዖታቸውን ከደው በዚች ሃይማኖት አመኑ ። የኦሪትን ሕግ ለመጠበት የሚያከ ብሩት ቅዳሜን ነበር ።

(፪) ገበያው የሚገኘው ፓብሳኒያስ እንደሚለው ከአቅሮጶሊስ በአርዮስ ፋጎስና በፒኔቆስ (ኮረብታ) መካከል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ያንጊዜም አዲሱን ስብከት ስለ «አዲሶቹ አማልክት» የሚባለውን እንግዳ የሆነውን ትምህርት ይሰሙት ዘንድ ወደውት ከበቡት ። ይኸውም ስለክርስቶስና ስለትንሣኤው የሚመሰክር በመሆኑ ኢጲቆሮሶችና ኢስጦኢኮች ባለ አቅማቸው ሙሉ የሚቃወሙት ትምህርት ነበር ። ይህንንም በሰሙ ጊዜ ከዚያ የነበሩት ሁሉ መገረም አደረባቸውና ይዘውት አርዮስ ፋጎስ ወደ ተባለው ፍርድ ቤት ወሰዱት ። እንዲህም ሲሉ (ይህን የምታስተምረውን አዲስ ትምህርት እናውቅ ዘንድ ይቻለናልን? ፡ አዲስ ነገር በጆሮአችን ታሰማናለህና ። እኛም ይህን ነገር ምን እንደ ሆን እናውቅ ዘንድ እንወዳለን» (፩)

ጳውሎስን የወሰዱበት ቦታ አርዮስ ፋጎስ ፡ ድንጋያማ የተንጠለጠለ ጉብታ በአቅሮጶሊስ ደቡብ የሚገኝ ነው ። እንዲህ ተብሎ የተሰየመው አርዮስ የሚባለው አምላክ በዚህ ቦታ በጥንት ዘመን ይመለክ ስለነበር ነው ተብሎ ይታመናል ። አርዮስ ፋጎስ የሚባለው የጥንት ፍርድ ቤት ከዚሁ በተያያዘው ኮረብታ ላይ በመገኘቱ እንዲህ ተብሎ ተጠራ ።

(፩) እነዚህ ከአምላኮች በታች ከሰው በላይ የሆኑትን መንፈሶች ነው አምላኮች የሚሏቸው ። እነሱም የማይታዩ ረቂቃን መንፈሶች ናቸው በመባል ይገመታሉ ።

አምላክ ፡ መንፈስና ሰው በመካከላቸው የሚበላለጡበት ምክንያት የሚከተለው ነው ።

ሀ አምላክ የሚበረ ጠው የማይሞትና የማይጐዳ በመሆኑ ነው ።

(ለ) መንፈስ ሕያው ሲሆን ይጐዳል ።

ሐ) ሰው ግን ይጐዳልም ይሞታልም (የማክሲሞስ ጤርዮስ ንግግር ፳፱ በ፪ተኛው መቶ ከክርስቶስ በኋላ የነበር ።



በሮማውያን ዘመን የአርዮስ ፋጎስ (ፍርድ ቤት) ሥልጣ
በወኑ ከፍ ያለ ሁኖ በከተማይቱ ብዙ የግዛት ዓይነቶች ያ
ናውን ነበር ። በአርዮስ ፋጎስ የነበረው ምክር ቤት ከግዛት ሌ
የፍርድ ሥራ ነበረው ።

የሚፈርደውም የሞት ፍርድ ብቻ ሳይሆን በከተማ
የሚደረገውን ማናቸውንም ወንጀል ሁሉ ነበር ። ብዙዎ
እንዳሉት ይህ አርዮስ ፋጎስ ያገኘው ሰፊ ሥልጣን ትምህር
ለመላይቱ ከተማ እንደበደል ሁና የተቆጠረበት ጳውሎስ ፡ ወ
ፍርድ ቤቱ በቀርብ ነገሩን ለማየት መብት ነበረው ። በዚ
ፍርድ ቤት ሕግ መሠረት እንዲህ ዓይነቱ ወንጀል ማለት አ
ግዳ አምልኮትን የሚሰብክ በእርግጥ በደልና ውርደት ሁ
የአቴንን ሕዝብ ስሜት የሚለውጥ በመሆኑ በሞት ፍር
ለመቅጣት ሥልጣኑ ይፈቅድለት ነበር ። ግን ተከሳሹ ስለትም
ህርቱ እየተጠያየቁ ተረጐመላቸው እንጂ ውርደት ባለመናገ
ከሳሾቹ በከተማችን ውርደት ይናገራል ብለው አልከሰሱትም
ጳውሎስን ሊዘልፍ እንደሚገባው ሰው ቈጥረውት ኢጲቆሮ
ችና ኢስጦኢኮች በአገኙት ቍጥር ስለአልታወቀው አምላ
ስለ ትንሣኤ ሙታንና ስለመጨረሻው ፍርድ ስለሚያስተም
ረው ትምህርት ይማለቁበት ነበር ።

ስለዚህ ጳውሎስ ከዚህ በታች እንደምናየው በትም
ርቱ ከላይ የጠራነውን ስለ ክርስቶስ ከሙታን መነሣት በላ
ጊዜ ። ልግጫና መሳለቅ በአለበት ንግግር « ስለዚህ በሌላ ጊ
እንሰማሃለን አሉት ። »

www.ethiopianorthodox.org

የእዚህ ንግግር ትርጓሜ ምን እንደሆን ጳውሎስ ስለገባው በሚቀጥለው እንደምናየው ከመካከላቸው ወጥቶ በመርከብ ወደ ቆሮንቶስ ሔደ ።

ድንቅ የሆነ የጳውሎስ ትምህርት

<u>በአርዮስ ፋጎስ ።</u>

ጳውሎስ በአርዮስ ፋጎስ መካከል ከቆመ በኋላ "አለ እናንተ የአቴና ሰዎች በሥራችሁ ሁሉ ጣዖት ማምለክ እንደ፡ታበዙ አያለሁ ። እኔ በዚህ ሳልፍ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበት የምታመልኩበትን መሠዊያችሁን አገኘሁ ይህንንም ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እገልጽላችኋለሁ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሌላውንም ነገር ሁሉ ይሰጣልና እንደ ቸግረኛ እጅ አያገለግለውም እርሱም በምድር ሁሉ ላይ ይኖሩ ዘንድ አሕዛብን ሁሉ ከአንድ ደም ፈጠረ ይኖሩበትም ዘንድ ዘመንና ዓመታትን ወስኖ ሠራላቸው ። ምናልባት እግዚአብሔርን ፈልገው እንደሆነ እርሱ ግን ከኛ ከሁላችን የራቀ አይደለም እኛ በርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖራለንም ከናንተ ቅኔ የሚቀኙ ብልሆች እኛ ዘመዶቹ ነን ብለው እንደተናገሩ ፤ እንኪያስ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆን በሰው አሳብና ብልሐት የተቀረጸ ወርቅም ብርም ደንጊያም ሆነ ይህ አምላክን ይመስላል እንል ዘንድ አይገባንም ። ያንንም የድንቁርናውን ወራት እግዚአብሔር አሳለፈው አሁን ግን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰዎችን ሁሉ አዘዘ ። በዚያ በአዘጋ



ጀው ሰው እጅ በዓለሙ ቅን ፍርድ የሚፈርድበትን ወስኖአልና ስለዚህ እርሱን ከሙታን ማስነሣቱ ሁሉን ወደ ሃይማኖት መለሳቸው ።"

ይህችንም ታሪካዊ የጳውሎስን ንግግር እንዳትጠፋ አብሮት ይደክም የነበር ወንጌላዊው ሉቃስ አቆያት (፩)

የጳውሎስ ንግግር ትርጓሜ ።

የአቴና ሰዎች ከማናቸውም ሕዝብ ሁሉ እግዚአብሔርን ፈሪዎችና ሃይማኖት ወዳጆች እንደሆናችሁ አያለሁ ። ስለምን? እከተማችሁ ከገባሁ አንሥቶ የአምልኮታችሁን አኳኋን በጥንቃቄ ስመለከት ከሁሉም መካከል አንድ እግዚአብሔርን ፈሪ መሆናችሁን የሚያሳይ መሠዊያ ለአልታወቀ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበት አገኘሁ ይህንኑ አምላክ ሳታውቁ እምታመልኩትን ላስረዳችሁ እነሆኝ ።

ቅዱስ ጳውሎስ አቴናን በጐበኘ ጊዜ አቴናውያን አባቶች ያቆዩትን በመከተል ሃይማኖተኞችና እግዚአብሔርን በመፍራት ከሌሎች ተሸለው ይታዩ ነበር በዚያን ጊዜ በሚያምር ፕላን የተሠሩ የአሠራራቸውም ቄንጥ የጐበኘን ሕሊና የሚማርክ የሆኑ የአማልክትና የአርበኞች መቀደሶች አቴናንና አካባቢዋን መንደሮች ያስጌጡ ነበር ።

እግዚአብሔር በማለት ንግግሩን ይቀጥላልዓለምንና በእሱም ላይ ያሉትን ሁሉ የፈጠረ የሰማይና የምድር ጌታ በእንድ ውሱን ቦታ እንደ እሊህ መቅደሶች ባለው የሰው እጅ በሠራቸው የእሱን ፍላጎት እንደአለው ብጤ ለመላው ለፍ

፩ የሐ ሥራ ፲፯ ፳፪ ፴፩

www.ethiopianorthodox.org

ጡር ሁሉ ሳይለይ ሕይወትንና እስትንፋስን የሚሰጥ ማንም በዚህ ይኖራል ። ብሎ የሚገምት የለም ።

በዚህ ንግግሩ ጳውሎስ በሰው ምስል የሆኑትን የግሪክ ችን አማልክት ከእውነተኛው አምላክ ጋር ያበላልጣል ። መን ንፈስና የዓለም ፈጣሪ ስለሆነ የሰው እጅ አያገለግለውም ሲል ዓይነት እዚህ ላይ ይታወቃል ። በዚህም ንግግር ኤጲቆሮሶችን የዓለምን መፈጠር የሚክዱትንና አምላክ ያለፈውንም መጭውንም ማወቁን የማያምኑትን እስጦኤኮችን የፈጣሪን ሥራ ለፍጡር ሰጥተው የሚያምኑትን በጣም ይቃወማቸዋል ።

ንግግሩን ይቀጥላል «እግዚአብሔር ከሁለት ሰዎች„ (ከአዳምና ከሔዋን) የሰውን ነገድ ሁሉ ፈጠረ ፈጥሮም በመላይቱ ምድር ላይ እያንዳንዱ ነገድና መሬቱን (መኖሪያውን) ወስኖ አስቀመጣቸው ይኸውም በምን ዓይነት ሁነው ፈጣሪያቸውን ፈልገው ያገኙት እንደሆነ ሊመረምሩ ነው ። ያገኙታልም ከኛ ከያንዳንዱ ሰው እርሱ እሩቅ አይደለምና ። ከኛም ሩቅ አለመሆኑን የሚያስረዳ ሕይወትን መንቀሳቀስንና መኖርን እምናገኘው ከእርሱ በመሆኑ ነው ። ከናንተ ቅኔ ተቀኚዎች «ወገኖቹ ነን» እንዳሉ ።

እላይ በተነገረው አኳኋን ሰዎች ሁሉ ከአንድ ቤተ ሰብ እንደ መገኘታቸው መጠን ፤ ቆይቶ እኩልነትንና ወንድምነትን አስገኘ ። ለዚህ ተቀዋሚ አቴናዎች እንደመሰላቸው ሰዎችን ለመለያ ወይም ለመበላለጥ ግሪኮችን አረመኔ (ጨካኝ) ይሉ ነበር ። (፩) ።

እግዚአብሔርን ከፈለጉት ዘንድ ለማግኘት ከበድ አይደለም ከኛ የራቀ አይደለምና ። ሕይወታችን ፤ እስትንፋሳችን ፤ በጠቅላላው የኑሮአችን ምንጭ መገኛው ከአምላክነቱ ነውና የእሱ ወገኖች እንደመሆናችን መጠን ።

ጳውሎስ ንግግሩን ይቀጥላል «የእግዚአብሔር ወገኖች (በእርአያው በአምሳሉ የተፈጠርን) ከሆን ፤ ከወርቅ ፤ ከብርና ከደንጊያ የተቀረጸ ሐውልት እሱ አምላክ ነው ። ብንል በእርግጥ አሳብ ጉድለኙነት ነው ። ይህ (ሐውልቱ) ምንም አይደል የእጅ ጥበብ ያላቸው ሰዎች ሐሳባቸው እንደመራቸው መጠን የቀረጹት የሰው እጅ ሥራ ነው ።»

በዚህ ንግግሩ አቴናዎችን ሊያስረዳ የፈለገው አምላክን የሰው እጅ በሠራው ጥበብ ብንመስለው የእሱ ወገኖች መሆናችንንና በአምሳሉ መፈጠራችንን መካዳችን ነው ሲላቸው ነው በሌላም ቦታ “ በእጅ የተሠሩ አማልክት አይደሉም „ (፪) እንደሚለው ።

«በእዚህ ድንቁርና ዘመን ማለት ሰዎች አምላክን በማያውቁበት ዘመን እግዚአብሔር ለሁሉ ሰው እንዲህ እያለ ይናገራል ። በየትም ቦታ ተገኝተው ንስሐ ቢገቡ እርሱ በዓለም በሰውነት የሚፈርድበት ወራት አለና ያንጊዜ ለያንዳንዱ እንደሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል ። ለሁላችንም በቅንነት መፍረዱ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ አረጋገጠልን» ። የዓለም ፈራጅ

(፩) በጥንት ዘመን ግሪኮች ከነሱ ተወላጅ ያልሆነውን ሁሉ አረመኔ አሕዛብ ብለው ነበር የሚጠሩ (፪) የግሪጎርዮ ቢዮስ የአቴን ከተማ ታሪክ ።



www.ethiopianorthodox.org

ያለውም ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ነው ።

እዚህ ላይ ሲደርስ ግሩም የሆነ ንግግሩ ተቋረጠ ። ስለ ምን በሬትም እንዳልነው ኤጲቆሮሶችና እስጦኤኮች ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ሲል የፊተኞቹ አፌዙ የኋለኞቹ ልግመ በሆነ ንግግር ይህንንስ በሌላ ጊዜ ትነግረናለህ በሚል ቃል አስተሐቀሩት ።

የሰሚዎቹንም ተቀዋሚነት ከአየ በኋላ በዚህ ምክን ያት ጳውሎስ ከመከከላቸው ወጣ ።

ይህ የተቋረጠው የመጨረሻው የጳውሎስ ንግግር ወደ ክርስቲያንነት የሚመልስበትን ዘዴ የተመላ ነው ። በዚህም ምክንያት አቴናዎች ብዙ አማልክት የሚያምኑበት ፣ የጣዖት አምልኮታቸው ከክርስቲያን ሃይማኖት ከፍ ያለ ሁኖ እንዲታይ አቅማቸው እስከ ፈቀደ ድረስ ደከሙ ።

"ቅዱስ ጳውሎስ በአቅሮጶሊስ በታች የክርስቲያንነትን ዘር ተከለ ። እሷም የሰውን የወደፊት ኑሮ ከትልቅ የፍልስፍና ሃይማኖትና ከጥንት የግሪክ ሥልጣኔ መከላከያ ሆነች ። ሙዋች ከሆኑ ሰዎች ወደ አቴን መጥተው አሳብ ከአቀረቡ ሁሉ እንደ ጳውሎስ ንግግር ሁኖ በዓለም የተደነቀ የለም ። የማይጠፋ የነቢይነት መልክ በአለበት ሁኖ ከፍልስፍናና በዚያም ዘመን ገና ያበራ ከነበር ከግሪክ የጥንት ሥልጣኔ ጋር ተቋቁሞ የሰውን ልጅ የወደፊት ኑሮ በሚገባ አጸደቀ ። ክርስቲያንነትን ለማስፋፋት ሐዋርያዊ ጉዞ ከአደረጉት ሁሉ ከዚህ ከጳውሎስ በአቴን በአቅሮጶሊስ የጥንት ማምለኪያና የሥልጣኔ ዓይኖች ገና ሳይከፈቱ ጥበብና ዕውቀት ያበሩበት በነበረው ቦታ ከተናገረው ብልጫ ድፍረት ያለበት የተናገሩ አይገኙም።„ (፩)

(፩) የሐዋ ሥራ ፲፱ ፳፮ ።



"ቅዱስ ጳውሎስ በአቴን የፈጸመው ሥራ ከዓለም ታሪክ መዝገብ ቦታ አገኘ ። ከፈላስፎች በቀር ሌላም ተቃዋሚ ነበረው ። ይኸውም የገዢናቸይቱ ከተማ የግሪክ ብዙ አመልክትና የሥልጣኔ መዲና ከሆነችቱ ከአቴን ብቻ ሳይሆን ፤ ከመላው ከግሪክ ነበር'' (፩) ።

ቅዱስ ጳውሎስ በአቴን ክርስቲያንነትን ለማስተማር ምቹ ቦታ እንዳላገኘ የተረጋገጠ ነው ። ምንም ፈላስፎች ያን ያህል቞ቢቃወሙት የአቴንን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ። ይህችንም የአርዮስ ፋጎስ ዲዮኒስዮስ በመጀመሪያ የአመነ አቴናዊና የመጀመርያ ኢጲስ ቆጶስ የሆነው አጸደቃትና ከፍ ከፍ አደረጋት ።

## ጳውሎስ በቆሮንቶስ ።

በመከከለኛው ዘመን በግሪክ ታሪክ እንደሚገኘው ቆሮንቶስ ከትልልቆቹ ከተሞች አንዷቱ ነበረች ስመ ጥሩነቷም ንግድንና ፋብሪካን አስፋፍታ ፤ የመርከብ ኃይል አግኝታ እጅግ ባለጸጋ ስለሆነች ነው ። የጥንት ምሳሌ (ተረት) እንደሚመሰክረው ኑዋሪዎቿ አስፈላጊ ለሆነው ለኑሮ ጣጣ የሚያወጡት ገንዘብ ግምቱ ከፍ ያለ ነበር ።"ለሁሉ ወደ ቆሮንቶስ መሔድ ቀላል አይደለም ።"

ይህ የቆሮንቶስ ይህንን ያህል እርምጃ ምክንያት ከምን እንደተነሣ ሲመረመር ከጂዮግራፊ አቀማመጥዋ የተነሣ ብዙ ሰዎች ይኖሩባት ስለነበር ነው ።

(፩) የፊተኛው የአቴን ሊቀ ጳጳሳት ህሪሶስቶሞስ (አፈወርቅ) የአቴን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፲ ፪ኛ መጽሐፍ ገጽ ፤ ፻፳፫

www.ethiopianorthodox.org

የተጌጠችና ብዙ ሰዎች የሚኖሩባት በመሆኑዋ ቅዱስ ጳውሎስን ስለአጓጓችው ፤ የአቴንን ቤተ ክርስቲያን ከመሠረተ በኋላ ። «አቴናን ለቆ ወደ ቆሮንቶስ መጣ» ። ከዚያም በራዕይ እንዲቆይና የእግዚአብሔርን ቃል እዚያ ለሚገኙት የጌታ ወገኖች ይሆኑ ዘንድ ላላቸው እንዲነገር ትእዛዝ ተሰጠው ።

በመጀመሪያ „ በየሰንበቱ በመስጊድ ያስተምር ነበር ,, ወገኖቹ አይሁድ አዲሲቱን ሃይማኖት ሲነቅፉና ሲቃወሙት ልብሱን እያራገፈ እንዲህ ይላቸው ነበር ። ደማችሁ በራሳችሁ ነው እኔ ንጹሕ ነኝ ከእንግዲህ ወዲያ ወደ አሕዛብ እሔዳለሁ በእውነቱም ወደ ቆሮንቶስ አሕዛብ ተመልሶ የሚያስተምርበትን በአንድ እግዚአብሔርን በሚፈራ ዮስጦስ በሚባል ቤት አደረገ ። በዚህም ትምህርቱ አያሌ ፍሬ ሰጠ ፤ ብዙ ጊዜ በአሕዛብ መካከል እንዲቀመጥ እስኪአጓጓው ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ ዓመት ከ፮ ወር ተቀመጠ ።

በዚያም በቆየበት ሰፊ ወራት የመጀመሪያይቱን የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን መሥራችና አናጭ ሆነ ።

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድና ቍጥራቸው በዛ ከአለ አሕዛብ የተሟላች ነበረች ። ከሊሁም በዕውቀት የተራቀቁና በአኗኗር ከፍ ያሉ ማለት ባለጸጎች ጥቂት አልነበሩም ።

ቆሮንቶስ ከላይ እንዳየነው በጂኦግራፊ አቀማመጧ ምክንያት የክርስቲያንነት መዲና ስለሆነች ቅዱስ ጳውሎስ ስለእርስዋ በጣም ያስብ ነበር ። ከጉብኝትም በኋላ ሁለቱ ወደ ቆሮንቶስ የላካቸው ጦማሮች ምን ያህሉን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን «የመልእክቱ ማኅተም» እስኪላት ድረስ ይጠነቀቅላት እንደ



ነበር ያሳያል ። በ፫ቱ መቶ ዓመታት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን የግዛቷ መዲና ቆሮንቶስ ነበረች ።

በፖለቲክ ረገድ ቆሮንቶስ የአካይያ (ግሪክ) ዋና ከተማ መሆንዋ ለቅዱስ ጳውሎስ ሳይታሰበው አልቀረም ። ስለዚህ ይመስላል የግሪክ ቤተ ክርስቲያን የኤጲስ ቆጶስ ወንበር እንድትሆን ያደረገው ፤ ከዚህም መከከለኛ ቦታ በደኅና ጊዜ ታሪክና እንዲሁም ሌሎች ጽሑፎች እንደሚመሰክሩ ክርስቲያንነት በሀገሪቱ ላይ በደንብ ተናኘ ።

የቅዱስ ጳውሎስ ምኞት በጉዞ የደከመበት በዚህ ሐዋርያዊ ሥራው በመላው ዓለም ክርስቲያንነት ዋና ሃይማኖት እንዲሆን ነው ። ግን ያሰበው ሳይፈጸም ይቀር ነበር ፲፬ቱ መልእክቶቹ ባይጻፉ ኑሮ ፤ ብዙ መንፈሳውያን መምህራን እንደገመቱት ፤ ቅዱስ ጳውሎስ የሰጠውን ሐሳቡን የፈጸመበት በጉዞው ሳይሆን በድርሰቱ (በመልእክቱ) ነው ሲሉ ሐሳባቸውን ይገልጣሉ ።

በርግጥ ትልቅ ነው የድርሰቱ ሥራ ትልቅ እንደሆነም መጠን ደግሞ የሐዋርያነቱ ሥራ ።

ተፈጸመ ።

www.ethiopianorthodox.org

| ተራ ቁጥር | ማውጫ ። | ገጽ |
|---|---|---|


መቅድም . . . . . . ፫

፩ኛ ክፍል ።

፩) ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት . ፲፫
፪) የደማስቆ ራዕይ . . . . . ፲፬
፫) ጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያ . . ፲፯
፬) የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ ሥራ ጠቅላላ
አስተያየት . . . . ፳
፩) የመጀመሪያ የቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ ፳፯
፪) ሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ . . . ፳፯
፫) ሦስተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ . . . ፳፯
፬) አራተኛው ሐዋርያዊ ጉዞ . . . ፳፱
፭) ፪ኛ ክፍል ቅዱስ ጳውሎስ በግሪክ ሀገር . ፴

ፊልጵስዩስ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ቤሪያ ፡ አቴን ፡ ቆሮንቶስ

፩) ጳውሎስ በፊልጵስዩስ . . . ፴
፪) ጳውሎስ በተሰሎንቄ . . . . ፴፪
፫) ጳውሎስ በቤሪያ . . . . ፴፬
፬) ጳውሎስ በአቴን . . . . ፴፭
፭) ድንቅ የሆነ የጳውሎስ ትምህርት በአርዮስ ፋጎስ ፵፬
፮) የጳውሎስ ንግግር ትርጓሜ . . . ፵፭
፯) ጳውሎስ በቆሮንቶስ . . . . ፵፱



ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271...
ዲያቆን ሰሎሞን
0911860113
0111/2716...
D.N Solomon Y...
www.ethiopianorthodox.org